# እግዚአብሔር

# እና

# ከሰው ልጆች

# ጋር ያለው ዕቅዱ

በኢ. ፍራንክ

## መቅድም

ይህ አጭር ጽሁፍ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ዕቅድ ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ለማስቀመጥ ያለመ ነው። በእርግጥ፣ ዋናው ጉዳያችን፣ ምንም እንኳን በነጥብ መልኩ ቢሆንም፣ አምላክነት የሚለው ርዕስ ነው። ለእያንዳንዱ የተወሰኑ ርዕሶች ጥቂት የመጻሕፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ከዚያ በኋላ እያንዳንዱ አንባቢ እውነትና የሚያስፈልገው ግልጽነት እስኪገኝ ድረስ በመጻሕፍ ቅዱስ ውስጥ በጥልቀት ለራሱ የመፈለግ እድል አለው።

አብዛኞቹ አይሁዶች በትንቢታዊው ቃል የተቀመጠውን የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ አላወቁም። እውቀቱም በክርስትና መመስረት ዉስጥ ጠፍቶ ነበር። ክርስትና ከጊዜ ወደ ጊዜ እውቅና ያገኘ ሃይማኖት ሆነ። ከሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ አይሁድ በሆኑት ሐዋርያት ከተቀመጠው መሠረት ተለየ። በእርግጥም፣ ያን ጊዜ ክርስቲያኖች አይሁዶችን አዳኛቸውን መሲሑን እንደገደሉ በአጠቃላይ ሲከሱ፣ ይህ የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል እንደሆነ አልተገነዘቡም ነበር። አይሁዶችም በግዳጅ ክርስቲያናዊ እንዲሆኑ አልፈቀዱም። ክርስትና ራሱን ከአይሁድ እምነት ባራቀበት ጊዜ፣ ክርስቲያኖችም ከብሉይ ኪዳን ርቀው በዚህም በነቢያት የተጣለውን ትክክለኛ የእምነት መሠረት ተዉት። አዲስ ኪዳንን ያለ ብሉይ ኪዳን መረዳት እንደማይቻል፣ ወይም ከእሱ ሊለይ እንደማይቻል የሚለው እውነታም ጠፍቶ ነበር። በመሆኑም ክርስትና ወደ እንግዳ፣ የተቀላቀለ ግን መሠረት ወደሌለው ሥነ-መለኮት ተዋኸደ። ይህ ሁኔታ እስከ ዛሬ ድረስ በክርስቲያናዊ ሃይማኖት ውስጥ ባሉ ቤተ እምነቶች ውስጥ በዓለም ዙሪያ ይገኛል።

ይህን ካየን በኋላ፣ ዝም ማለት አይቻልም። እውነትን ከልብ የሚፈልግ ሁሉ እውነቱን የማወቅ እና እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የሚናገረውን በራሱ ተረድቶ ራሱን የማሳመን መብት አለው። በሁሉም ነገር፣ ጌታ ኢየሱስ ወደ ብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ጠቅሷል፣ እና ፍጻሜውን እንዲረዱት የደቀ መዛሙርቱን አእምሮ ከፍቷል (ሉቃስ 24)። ሐዋርያትም ብሉይ ኪዳንን ብቻ ጠቅሰዋል። በእርግጥም፣ አዲስ ኪዳን በሐዋርያት ዘመን አልተጻፈም። እግዚአብሔርንና ዕቅዱን ለመረዳት፣ ከብሉይ በትንቢት ከተቀመጠው ድልድይ ወደ አዲስ ኪዳን መሻገር አለብን።

ስለ አምላክ የሚጽፍ ማንኛውም ሰው በጣም ጥንቃቄ የሚፈልግ ጉዳይን እየተመለከተ ነው። ልዩነቶቹ በተለምዶ የታወቁ ናቸው። አንዳንዶች እግዚአብሔር አንድ አካል ነው ብለው ያምናሉ፣ ሌሎች ደግሞ በሁለት እንዳለ፣ እና ሌሎች ደግሞ ሦስት አካል ያለው አካል እንደሆነ ያምናሉ። ስለ አምላክ ያሉትን ብዙ ሌሎች ግምቶችን ለማካተት አንሞክርም።በሚከተሉት ገፆች ላይ የተመለከቱት ስእሎችን መመልከት ነገሩን ግልጽ ያደርገዋል። ምስሎች እንደሚያሳዩት ስለአምላክ የሰው እይታዎች እንዴት እንደሆኑ ግልጽ ያደርግልናል።

በነቢያት ዘመን እና በኋላም በሐዋርያት ዘመን፣ ስለ አምላክ ምንም ዓይነት ግምት አልነበረም። በመገለጥ እና በግምት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። መጽሐፍ ቅዱሳዊው መሠረት ከተተው በኋላ


ብቻ የሰው ሀሳቦች የበላይ ሆኑ እና የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጠፋ። "የመሰናከያ ድንጋይ" ክርስቶስ ነበር እና እስከ ዛሬ ድረሰም እንደዚያዉ ነዉ ። አሃዳዊዎች በአንድ አምላክ ያምናሉ፣ ግን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትነት ይክዳሉ። ከዚህ ተቃራኒው ሥላሴ የሚለው አስተምህሮ ሲሆን ይህም እግዚአብሔርን በሦስት አካላት ያመለክታል። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ከመታደስ በኋላ በእግዚአብሔር መንግሥት እድገቶች ውስጥ የተሳተፉት በሌሎች አስተምህሮቶችች ታዋቂ ሆኑ፣ ነገር ግን ይህን በጣም አስፈላጊ ርዕስ አልተመለከቱትም። እስከ ዛሬ ድረስ፣ ባህላዊው ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ አስተምህሮቶች ከትዉልድ ትዉልድ በቅብብል ተላልፈው በተለያዩ ቤተእምነቶች ተቀባይነት አግኝተዉ እዚህ ደርሰዋል። ስለ እግዚአብሔር ያላቸው እውቀት ለአንዳንዶች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ በሚከላከሉበት መንገድ ይታያል።

የመጀመሪያውን ትርጉም በተሻለ ለመረዳት፣ የዕብራይስጥ ቃላት ኤሎሂም (ELOHIM)፣ ያህዌ (YAHWEH) እና ያህሹአ (YAHSHUA) ጥቂት ጊዜ ጥቅም ላይ ውለዋል። ስሞች ሁልጊዜ ትርጉምን ይገልጻሉ። በእርግጥም፣ እውነተኛ ግልጽነት የሚመጣው ዕብራይስጥ ወይም የግሪክ ቋንቋ በማወቅ ሳይሆን፣ በነቢያትና በሐዋርያት ላይ ባረፈው እና ባነሳሳው በዚያው መንፈስ ብቻ ነው። ያ እነሱ ያዩትን እንድናይ፣ የሰሙትን እንድንሰማ፣ እና እንዴት እንደተረዱ እንድንረዳ ብቸኛው መንገድ ነው።

አንዳንዶች "መናፍስትን መርምሩ!" የሚል ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ እና ስለ ሌሎች ብቻ ያስባሉ። ሁሉም ሰው በግሉ ሊተገብረው ይገባል። በዚህ ሁኔታ፣ ሁሉም ሰው የተወረሱትን ባህላዊ ትምህርቶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማነፃፀር እድልን መጠቀም አለበት። የሚያገለግሉት እና የሚሰሙት ሰዎች የቃሉ ትርጓሜዎች እየተሰበኩ እንጂ የመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር ቃል ራሱ እየተሰበከ አለመሆኑን አያውቁም። በእግዚአብሔር የተላኩ እና የተሾሙ ሰዎች ቃሉን አምጥተውልናል፤ የነገረ መለኮት ምሁራን ለሁሉም የተለያዩ ትርጓሜዎች ተጠያቂ ናቸው። ማንም በዚህ ማብራሪያ ሊጎዳ አይገባም። ብቸኛው ዓላማ የሕያው እግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ማገልገል እና መርዳት ነው።

ሁሉም አንባቢዎች በብዙ በረከት ይባረኩ

ክሬፌልድ፣ አፕሪል 1986 አርታኢዉ




ከላይ ያለው ስዕል አብ በትር ይዞ፣ ወልድ መስቀል ይዞ፣ እና መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ከእነሱ በላይ እየሰፈፈ እንዲታይ የታሰበ ነው።

በእነዚህ ስዕሎች ላይ ምን ታያለህ? – አንድ አምላክ ወይስ ሶስት ?

ከታች ያሉት ሶስቱ ሰዎች አንድ አምላክ ለመስራት ነዉ። ይህ እንዴት ይቻላል?






"አምላክ በሒሳብም ሊገለጽ ወይም ሊሳል አይችልም።"



The Trimurti. A depiction of the Hindu Trinity: Brahma the Creator, Vishnu the Preserver and Mahesh the Destroyer

ለአንዳንዶች የሂንዱ ሥላሴ ጥንታዊ ስዕል ማየቱ አስገራሚ ሊሆን ይችላል። ስለ እግዚአብሔር የሰው ልጅ አስተሳሰቦች ከናምሩድና ባቢሎን ዘመን ይጀምራሉ። እነዚህ ሀሳቦች እንዴት በኋላ በክርስትና ተቀባይነተ እንዳገኑ መገመት አይቻልም። ሥዕሎቹ በአስትምህሮ የሚያሳዩትን በትክክል የሚረዳ ሰው ከቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኘውን ግልጽ ማብራሪያ ያደንቃል፤ ይህ ደግሞ እጅግ በጣም በአስቸኳይ የሚያስፈልግ ነው።

# አምላክ

የአይሁድ፣ የክርስትና እና የመሐመዳዊ ሃይማኖቶች "አሀዳዊ" ተብለው ይጠራሉ፤ ይኸውም የአንድ አምላክን መኖር ያምናሉ። ነገር ግን ስለ አምላክ ፍጹም የተለያየ ውጤት ላይ ደርሰዋል። ትምህርቶቻቸውና ተስፋዎቻቸው እርስ በርስ ፍጹም ይጋጫሉ።

የመነሻው ቦታ አንድ ከሆነ የተለያዩ እድገቶችን እንዴት ማስረዳት ይቻላል? እግዚአብሔር ራሱን በበቂ ሁኔታ ግልጽ አላደረገምን? አይሁድ እንደ ተመረጡ ምስክሮቹ የእርሱን መገለጥ አላወቁምን? ክርስቲያኖች በተሳሳተ መንገድ ተርጉመውታልን? ሙስሊሞችስ በቀድሞው ሕግ ግራ ተጋብተው ሙሉ በሙሉ ችላ ብለውታልን? እግዚአብሔር ስለ ራሱ በቂ ምስክርነት ሰጥቷል፣ ነገር ግን በቃሉ ውስጥ ያለዉን የእርሱን ምስክርነት፣ በሁሉም ነቢያቱ አማካኝነት በፍጹም ስምምነት የተሰጠውን፣ እና በጻህፍትና እነሱ ከእሱ የሠሩትን መለየት አለብን። በእውነት የሚያምን ሰው እግዚአብሔር በራሱ ቃል የተናገረውን ብቻ ዋጋ ይሰጣል። ሰዎች ስለ እርሱና ስለ ቃሉ የሚሉት ነገር አስፈላጊ አይደለም፣ ነገር ግን የተለያዩ ቤተ እምነቶችንና ሃይማኖቶችን ለመፍጠር ትክክለኛው ምክንያት ያ ነበር። ጌታ ራሱን እኛ በምንፈልገው መንገድ ሳይሆን እርሱ ራሱን እንዳለ ማስተዋወቅ ይፈልጋል።

በነቢዩ ኢሳይያስ አማካኝነት እንዲህ ሲል ተናገረ፦ "እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር፣ የመረጥሁትም ባሪያዬ ሆናችሁ ታውቁኝና ታምኑኝ ዘንድ፣ እኔም እርሱ እንደ ሆንኩ ታስተውሉ ዘንድ፤ ከእኔ በፊት ምንም አምላክ አልተፈጠረም፣ ከእኔ በኋላም አይሆንም። እኔ ነኝ፣ እኔም ብቻዬን ጌታ ነኝ፣ ከእኔ በቀርም አዳኝ የለም።" (ምዕራፍ 43: 10-11)። እውነተኛ ምስክር የሆነ ነገር አይቶና ሰምቶ መሆን አለበት፣ ከመመስከሩ በፊት ከተከሰተው ክስተት ጋር መገኘት አለበት። ቃሉ ወደ ነቢያት መጣ። እግዚአብሔር ያዩትን፣ የሰሙትንና ያጋጠሟቸውን ነገሮች ለመመስከር ተጠቀመባቸው። የእስራኤል ሕዝብ በጋራ "ባሪያዎች" እና "ምስክሮች" ተብለው ይጠራሉ። በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ አማካኝነት የእግዚአብሔርን የራሱን እጅግ ቅዱስ ምስክርነት እንዲሸከሙ ተመርጠዋል። የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ የእግዚአብሔርን ራስን መገለጥ መመስከር ነው፣ ይህም እስከ ዛሬ ከታወቁት ታላላቅ ምሥጢራት በላይ የሆነዉን ሚስጥር እዉን ማድረግ ነው።

ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ እናነባለን፦ "ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል ሰው ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጅ ፤ እርሱ ብርሃን አልነበረም።" (ዮሐንስ 1: 6-8)። እጅግ ታማኙ ምስክር ራሱ ጌታ ነበር፣ እርሱም እንዲህ አለ፦ "ከላይ የሚመጣ ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሆነ የምድር ነው፣ የምድርንም ይናገራል። ከሰማይ የሚመጣዉ ከሁሉ በላይ ነው። ያየውንና የሰማውንም ይህን ይመሰክራል፤ ምስክሩንም የሚቀበል የለም። ምስክሩን የተቀበለ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ አተመ።" (ዮሐንስ 3: 31-33)። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጻፈ፦ "እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን፣ ሰው ሁሉ ግን ውሸታም ነው።" (ሮሜ 3: 4)። በኢሳይያስ 43 ላይ ከተገኘው ጋር ተመሳሳይ የሆነ አጻጻፍ በዚያን ቀን የዓይንና የጆሮ ምስክሮች

ለሁኑት "ለሐዋርያት" ፣እነርሱም ከመሲሑ ጋር የተከሰተውን ነገር ሁሉ የተለማመዱ ለነበሩት ተነገረ፡- "…እናንተም በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ ሁሉ፣ በሰማርያም፣ እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።" (ሐዋ. 1: 8ለ)።

ሐዋርያትም ለዚህ በተናጠል መስክረዋል። ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "ከመጀመሪያው የነበረውን፣ የሰማነውን፣ በዓይኖቻችን ያየነውን፣ የተመለከትነውን፣ እጆቻችንም የዳሰሱትን፣ ስለ ሕይወት ቃል … ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ እንገልጻለን…" (1ኛ ዮሐንስ 1: 1-3)። ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጠ፡- " የእርሱን ግርማ በዓይናችን አይተን እንጅ በብልሃት የተፈጠረዉን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታውቅናችሁ ።" (2ኛ ጴጥሮስ 1: 16)።

የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ስምምነት እና የነቢያትና የሐዋርያት ሙሉ በሙሉ መገጣጠም ለሁሉም የሚያስደንቅ መሆን አለበት። ለዘላለም አንድ ዓይነት አምላክ ይናገራል እና ይሠራል። ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "…ስለእግዚአብሔር ቃል እና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ያየውንም ሁሉ መሰከረ" (ራእይ 1: 2)። ነቢያትና ሐዋርያት ፈጽሞ "እኔ እንደዚያ አስባለሁ"፣ "ምናልባት"፣ "ይሆን ይሆናል" ወይም "ሊሆን ይችላል" አላሉም። በቃላቸውና በምስክርነታቸው ፍጹም እርግጠኝነት አለ፣ ምክንያቱም ሰምተዋል፣ አይተዋል፣ አጋጥሟቸዋል።

በዚህ ገለፃ ውስጥ የብዙ ሊቃውንትና የነገረ-መለኮት ምሁራን ሃሳቦችን፣ ወይም የሚጽፉትንና የሚያብራሩትን አናካትትም። እኛ የምንጠብቀው የመለኪያ በትረ ምሰሶ እና ብቸኛ መሠረት ከሆነው ከመጻሕፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር ብቻ ነው። ማንም ጥልቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢራትን ሊረዳ አይችልም፤ ይህ እውነት ነው። ምክንያቱም በ1ኛ ቆሮንቶስ 2: 14 ላይ የተጻፈው እስከ መጨረሻው ይገለጻል፡- "ተፈጥሯዊ ሰው የእግዚአብሔርን መንፈስ ነገር አይቀበልምና፤ በእርሱ ዘንድ ሞኝነት ነውና፣ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀዉ አይችልም።"

ጳውሎስ ደግሞ አይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን ወዘተ ነገሮች አስመልክቶ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "እግዚአብሔር ግን በመንፈሱ ለእኛ ገለጠልን፤ መንፈስ ሁሉን ይመረምራልና፣ የእግዚአብሔርንም ጥልቅ ነገር እንኳ።" (1ኛ ቆሮንቶስ 2: 10)። በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት የአንዱን ሁሉን ቻይ አምላክ ምሥጢራዊ የተደበቀ ግን የተገለጠ ጥበብን እናውቃለን (1ኛ ቆሮንቶስ 2: 7)።

እውነተኛ አማኞች በዮሐንስ 16: 13 መሠረት ወደ ቃሉ እውነት ሁሉ ይመራሉ፡- "…ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፣ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።" የሮሜ 8: 14 አባባል አሁንም እውነት ነው፡- "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።" የሰው መንፈስ ወደዚያ ከተፈጥሮ በላይ ወደ ሆነ ልኬት መግቢያ የለዉም።

እግዚአብሔር ከዘላለም ነው፡- እርሱ መንፈስ ነው (ዮሐንስ 4: 24)። እስኪወጣ ድረስ በራሱ ግርማ ውስጥ ተሰዉሮ ነበር። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6: 16 ላይ ስለ እርሱ እንዲህ እናነባለን፡- "…እርሱ ብቻ

የማይሞት ነው፣ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ ማንም ያላየውና ሊያየው የማይቻለው፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን። አሜን።" ዘላለም ፈጽሞ አልጀመረም፣ ስለዚህም ፈጽሞ ሊያልቅ አይችልም። እግዚአብሔር ከዘላለም ሲወጣ፣ ጊዜ ተጀመረ። መጽሐፍ ቅዱስ ያንን ቅጽበት "መጀመሪያ" ብሎ ይገልጸዋል። በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር፣ ያልታወቀውና የማይታየው፣ ከግርማው ሙላት ወጥቶ በሚታይ መልክ፣ በቲኦፋኒ(theophany)፣ ማለትም በመንፈሳዊ አካል ታየ።

በዘፍጥረት 1: 1 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።" ያ "መጀመሪያ" ማብቂያ የሌለው ዘላለም አልነበረም ነገር ግን እግዚአብሔር ታላቅ ዕቅዱን መፈጸም የጀመረበትን የጊዜ መጀመሪያ ያመለክታል። ዮሐንስ እግዚአብሔር በተግባር በነበረበት በዚያ ቅጽበት እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" (ዮሐንስ 1: 1)። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና በውስጡ ያለውን ሁሉ ፈጠረ፣ ከዚያም ምድርንና ባሕርን፣ በውስጡ ያለውንም ሁሉ ፈጠረ። "ምድር" ተብላ የምትጠራው ይህች ፕላኔት ቅርጽ የሌላትና ባዶ ነበረች፤ በምድር ላይ ብርሃንና ሕይወት አልነበረም። ጨለማ በጥልቁ ላይ ነበረ። ከዚያም እግዚአብሔር ተናገረ፡- "'ብርሃን ይሁን' አለ፤ ብርሃንም ሆነ።" (ዘፍጥረት 1: 3)። ሁሉም ነገር በተነገረ በቃሉ ኃይል ወደ መኖር መጣ። ቃሉ በራሱ ውስጥ የፈጠራ ኃይል አለው (ዕብራውያን 11: 3)። ግርማ ሞገስ ያለዉ የአጽናፈ ሰማይ ፈጠራ የፈጣሪውን ግርማ ይመሰክራል።

ማንም ሰው እግዚአብሔርን በአእምሮ እውቀቱ ለመረዳት መሞከር የለበትም፣ እንዲሁም ማንም በነገረ መለኮታዊ ቃላት ሊያስረዳው መሞከር የለበትም። እርሱ ከሁሉ መረዳት በላይ ነው፣ እና ከመቼውም ጊዜ በላይ ከሚኖረው እውቀት በላይ ነው፣ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈው፡- "...እነሆ፣ ሰማይና ከሰማያት በላይ ያለዉ ሰማይ እንኳ ሊይዝህ ዘንድ አይችልም።" (1ኛ ነገሥት 8: 27)። በኢሳይያስ 66: 1 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ሰማይ ዙፋኔ ነው፣ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት።" ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ሁሉንም ነገር ይሞላል፤ እርሱ ወሰን የሌለውና ሁሉን ቻይ ነው። የማይታወቅ፣ የተደበቀ፣ ስም ወይም ቅርጽ የሌለው አምላክ ሆኖ አልቀረም–ጊዜ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ራሱን በተለያዩ መንገዶች አሳውቋል።

## አንድ አምላክ–ብዙ ስሞች

በብሉይ ኪዳን መጀመሪያ የምናገኘው የዕብራይስጥ ቃል ኤሎሂም (Elohim) ሲሆን ይህም በመጽሐፍ ቅዱሳችን "እግዚአብሔር" ተብሎ ተተርጉሟል። ኤሎሂም የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ነው የሚቀርበው፣ በውስጡ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸውን የተለያዩ ባህሪያትን ስለያዘ – እንደ ፈጣሪ፣ ደጋፊ፣ አዳኝ፣ ወዘተ። አምላክ ሲባል ሁልጊዜ ኤል (El)፣ ኤላህ (Elah) እና ኤሎሂም የሚሉትን ቃላት እናገኛለን። የተጣመሩት ስሞች የእግዚአብሔርን ሙሉነት ይገልጻሉ። በዘፍጥረት 14: 18 ላይ፣ እግዚአብሔር ራሱን ኤል ኤልዮን (El Elyon) ማለትም "ልዑል" በማለት ገለጠ።

ለአብርሃም ጌታ አምላክ ኤል ሻዳይ (El Shaddai) ማለትም "ሁሉን ቻይ አምላክ" ሆኖ ታየ (ዘፍጥረት 17: 1)። ይህ እግዚአብሔር የሚጠብቅ፣ ጥንካሬን የሚሰጥ፣ ለሁሉ በቂ መሆኑን ያሳያል። ኤል ሻዳይ የሚለው ቃል በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ከሠላሳ ጊዜ በላይ ይገኛል።

በዘፍጥረት 21: 33 ላይ፣ የዕብራይስጥ ቃል ኤል ኦላም (El Olam) እናገኛለን፣ ይህም በቀላሉ "ዘላለማዊ አምላክ" ማለት ነው። በኢሳይያስ 9: 6 ላይ፣ ስለ ኤል ጊቦር (El Gibbor) እናነባለን፣ ይህም "ኃያል አምላክ" ማለት ነው። ይህ መግለጫ በጣም ልዩ ጠቀሜታ አለው፣ ምክንያቱም አዳኝ ተብሎ ተስፋ ከተጣለበት ጋር በተያያዘ የተሰጠ ነው። ይህ በራሱ አምላክነቱን ያረጋግጣል። አውዱን እናንብብ፦ "ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅ ተሰጥቶናልና፣ አለቅነትም በጫንቃዉ ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ (ዕብራይስጥ፡ ኤል ጊቦር)፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።" (ኢሳይያስ 9: 6)። እንደምናየው፣ የእግዚአብሔርና የነቢያቱ ምስክርነት አንድ ነው፣ እርሱ ራሱ እንደ "እማኑኤል" ማለትም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" (ኢሳይያስ 7: 14፤ ማቴዎስ 1: 22-23) እንደሚመጣ ይናገራሉ።

ከኤሎሂም ጋር ተያይዞ ያህዌ (Yahweh) (የመጀመሪያው፡ YHWH) የሚለው ቃልም ጥቅም ላይ ይውላል። ያህዌ በቀላሉ " ዘላለማዊ እና ራሱ በራሱ ህላዌ ያለዉ" ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን "ጌታ" ተብሎ ተተርጉሟል። ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ኤሎሂም የሚለውን ቃል ብቻ ተመዝግቧል። እዚያ እግዚአብሔር ሰውን በመንፈሳዊ አካል በራሱ መልክ ፈጠረው። በዘፍጥረት 2: 4 ላይ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የሁለቱን ቃላት ጥምረት "ጌታ አምላክ" (ኤሎሂም ያህዌ) እናገኛለን። ይህ ከምድር አፈር ከተፈጠረው ሰው ጋር የተያያዘ ነው፣ በሥጋ አካል ውስጥ ሲቀመጥ።

የያህዌን ስም ጠቀሜታ እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን አዳኝ በሆነ ጊዜ አሳወቀ ። ስለዚህ እንዲህ እናነባለን፦ "እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው፦ እኔ ያህዌ (ጌታ) ነኝ፤ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ በኤል ሻዳይ (ሁሉን ቻይ አምላክ) ስም ተገለጥኩላቸው፣ ነገር ግን በስሜ በኤሎሂም ያህዌ አልታወቅኁቸውም ነበር።" (ዘፀአት 6: 2-3)። ነቢዩ ሙሴ ያህዌ የኤሎሂም የሚታይ መገለጥ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ቶራ ሲጻፍ – የሙሴ አምስቱ መጻሕፍት – ሁልጊዜ በትክክለኛው ግንኙነት ውስጥ ትክክለኛው ስም ይመረጥ ነበር።

እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘፍጥረት 15: 13-16 በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት፣ የእስራኤል ሕዝብ ሊድኑ ነበር። የመዳናቸው ታሪክ በዘፀአት 6-13 ውስጥ ሊነበብ ይችላል። ያህዌ የሚለው ስም በዚያ ግንኙነት ጥቅም ላይ ውሏል፣ ምክንያቱም በእርሱ ጌታ ለሙሴ ተገለጠ፣ ሙሴም በእግዚአብሔር ሥር ከግብጽ መውጣቱን የሚመራ ነበር። ስለዚህ ያህዌ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስም ሆነ። በዚህ ስም እስራኤል ይባረክ ነበር (ዘኁልቁ 6: 22-27)።

## ሰባቱ የተጣመሩ ስሞች

ኤሎሂም በተገቢው ግንኙነት ጥቅም ላይ እንደሚወል ሁሉ፣ ከያህዌ ስም ጋርም ተመሳሳይ ነው። የሚያስፈልገው ሁሉ በዚያ ስም ተገልጿል። ያህዌ-ይሬ – "ጌታ ያዘጋጃል" (ዘፍጥረት 22: 7-14)፤ ያህዌ-ራፋ – " ጌታ ፈዋሹ" (ዘፀአት 16: 26)፤ ያህዌ-ኒሲ – "ጌታ አርማየ ነው" (ዘፀአት 17: 8-15)፤ ያህዌ-ሻሎም – "ጌታ ሰላማችን ነው" (መሳፍንት 6: 24)፤ ያህዌ-ጺድኬኑ – "ጌታ ጽድቃችን ነው" (ኤርምያስ 23: 6)፤ ያህዌ-ሻማህ – "ጌታ በዚህ አለ" (ሕዝቅኤል 48: 35)፤ ያህዌ ጸባኦት – "የሠራዊት ጌታ" (1ኛ ሳሙኤል 1: 3)። እነዚህ ስሞች ሁሉንም ባህሪያቱን ይገልጻሉ። እርሱ ሁሉ ነገር ነው።

አይሁዶች በጸሎታቸው ውስጥ አዶናይ (Adonai) እና ኤሎሂም የሚሉትን ስሞች ይጠቀማሉ። ምናልባትም በአሞጽ 6: 10 ላይ እንዳስጠነቀቀዉ፣ "... ዝም በል፤ የጌታን ስም እንጠራ ዘንድ አይገባንም ይለዋል ።" የሚለውን ስም ለመጥራት ስለማይፈልጉ ይሆናል። አዶናይ የሚለው ቃል "ጌታና አለቃ" ማለት ነው። ይህ ቃል ለክርስቶስም በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ይውላል፣ በዮሐንስ 13: 13፤ ሉቃስ 6: 46 ወዘተ ላይ እንደሚገኘው። ከአዶናይ ቃል ጋር የተያያዘ ምንም ዓይነት ጥምረት የለም፣ እንደ ኤሎሂም እና ያህዌ። በዘፀአት 4: 10 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "ሙሴም ያህዌን (ጌታን) እንዲህ አለው፡- አቤቱ አዶናይ (ጌታዬ)፣ እኔ አንደበተ ርቱዕ አይደለሁም... በንግግር የዘገየሁ፣ ኮልታፋ ነኝ።" ሙሴ እግዚአብሔር ለተወሰነ አገልግሎት እንደጠራው ያውቅ ነበር። ስለዚህ፣ ጌታን በአዶናይ ስም ጠራው። በቀላሉ በጌታና በአለቃ መካከል ያለውን ግንኙነት እና ትእዛዙን እንደ አገልጋይ መታዘዝ ያለበትን ሰው ይገልጻል።

ያህዌ አይድለም ራሱን እንደ ኤሎሂም የገለጠው ፤ ኤሎሂም ነዉ ራሱን እንደ ያህዌ ያሳወቀው ነበር። በዘላለም ዉስጥ፣ ኤሎሂም ብቻ ነበር። ከዚያም ያህዌ ሆኖ ታየ። በዚህም መልኩ ተገልጦ፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ ተናገረ እና ሰራ። ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እንደ ጌታ ይገናኘናል – ሁለት ስሞች፣ ሁለት መገለጦች፣ ግን ሁልጊዜ አንድና ተመሳሳይ አካል። ይህ በአዲስ ኪዳን እርሱ ራሱን በመገለጥ ረገድ በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው። ወልድ ራሱን እንደ አብ አልገለጠም፣ ነገር ግን አብ በወልድ ተገለጠ። ያ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው።

በእግዚአብሔር ውስጥ ብዙ አካላት እንዳሉ ያመነ ነቢይ ወይም ሐዋርያ አልነበረም። በተቃራኒው፡ አጽንዖቱ በአንድ አምላክ መኖር ላይ ነበር። በሙሴ አማካኝነት ጌታ ስለ ራሱ እንዲህ ሲል መሰከረ፡- "እስራኤል ሆይ ፤ስማ። አምላካችን ጌታ አንድ ጌታ ነው፤ አምላክህን ጌታን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ።" (ዘዳግም 6: 4-5)። ዘላለማዊው ራሱ ስለተናገረው ይህ ዘላለማዊ እውነት መሆን አለበት። በዘዳግም 4: 35-39 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "ጌታ እርሱ አምላክ እንደሆነ ታውቅ ዘንድ ይህ ለአንተ ተገለጠልህ፤ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። ድምፁን እንድትሰማ ከሰማይ አሰማህ፣ ሊያስተምርህም፣ በምድርም ላይ ታላቅ እሳቱን አሳይህ፣ ቃሉንም ከእሳቱ መካከል

ሰማህ... ስለዚህ ዛሬ እወቅ፣ በልብህም አስብ፣ ጌታ እርሱ በላይ በሰማይ፣ ከታችም በምድር አምላክ እንደሆነ፤ ሌላ የለም።"

አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ያለው፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ በሰማይና በምድር በተለያዩ መንገዶች ራሱን መግለጥ ይችላል። ድምፁ ከላይ ሊታይ ይችላል፣ እርሱ ግን በምድር ላይ ሆኖ፣ ለምሳሌ በሲና ተራራ ላይ። ስለዚህ በነህምያ 9: 13 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "በሲና ተራራም ወረድህ፣ ከሰማይም ተናገርካቸው፣ ትክክለኛ ስርአቶችን፣ እውነተኛ ሕግጋትን፣ መልካም ደንቦችንና ትእዛዞችን ሰጠሃቸው።" ማጣቀሻው ለታላቁ የሕግ አሰጣጥ ክስተት ነው። ጌታ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ እሳት በተራራው ላይ ወረደ፣ ነገር ግን በምድር ላይ እያለ በታላቅ ድምፅ ከሰማይ ተናገረ። የተገኙት ሰዎች የክስተቱ ዓይንና ጆሮ ምስክሮች ሆኑ እና ፈሩ። "ሕዝቡም ሁሉ ነጎድጓድን፣ መብረቅን፣ የመለከት ድምፅንና ተራራው ሲጨስ አዩ፤ ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ ተንቀጠቀጡ፣ ርቀውም ቆሙ። ሙሴንም፦ አንተ ተናገረን፣ እኛም እንሰማለን፤ እንዳንሞት ግን እግዚአብሔር  አይናገረን አሉት።" (ዘፀአት 20: 18-19)።

## የጌታ መልአክ

ሙሴ የጌታ መልአክ በእሳት ነበልባል ሆኖ እንደ ታየው ይነግረናል፣ ይህም በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ እንዳየው ነው (ዘፀአት 3: 2-6)። በቁጥር 4 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "ጌታም (ያህዌ) ሊመለከት ዞር እንዳለ ባየ ጊዜ፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከቁጥቋጦው መካከል ጠራው እንዲህም አለ፦ ሙሴ! ሙሴ! እርሱም፦ እነሆኝ አለ። እርሱም፦ ወደዚህ አትቅረብ፤ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ። ደግሞም፦ እኔ የአባትህ አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለ። ሙሴም ፊቱን ሸፈነ፤ እግዚአብሔርን ለመመልከት ፈርቶ ነበርና።"

በጣም የሚገርም ነው፣ ነገር ግን በዚህ ዘገባ ውስጥ "...ጌታ አየ..."፣ "...እግዚአብሔር ጠራ..."፣ እንዲሁም "የጌታ መልአክ" ሲገለጽ እናነባለን። ማን ነበር እዚያ? በእርግጥ ሦስት አካላት ሳይሆን፣ አንድና ያው አካል በሦስት የተለያዩ ቃላት የተገለጸ ነው። የጌታ መልአክ በቀላሉ የእግዚአብሔር የሚታይ መገለጥ በመልአክ ቅርጽ ነው። በዚህ መንገድ ነው በኤደን ገነት ውስጥ እንደ ያህዌ ሲመላለስና ለአዳም ሲናገር የነበረዉ ፤  በዚህ መንገድ ነው አብርሃምን የተገናኛዉ። በዘፍጥረት 18 መሠረት፣ ሁለት መላእክትን አስከትሎ ወደ እርሱ መጣ፣ እነዚያም በኋላ ወደ ሰዶም ሄዱ። እዚያ እንዲህ እናነባለን፦ " በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ጌታም በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት።" (ዘፍጥረት 18: 1)። አብርሃም የሰማያዊዎቹ ጎብኚዎች እግር እንዲታጠብም ጠየቀ። ለእነሱ ምግብም አዘጋጀ። ሌሎቹ ሁለቱ መላእክትም በሰው ቅርጽ ነበሩ፤ እንዲያውም በሰዶም የነበሩት በአጋንንት የተያዙት ግብረ ሰዶማውያን እነርሱን ለመያዝ ሞክረዋል። ጌታ ከአብርሃም ጋር ቆይቶ ከእርሱ ጋር ረጅም ውይይት አደረገ። ጌታ የተገለጠበት የመልአክ ቅርጽ በትክክል የሰው ቅርጽ ነበር። እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረ!

በዘፀአት 33: 11 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "እግዚአብሔርም ሰዉ ከጓደኛዉ ጋር እንደሚነጋገር ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት ይነጋገር ነበረ ።" ሙሴ ጌታ ከእርሱ ጋር እንዲሄድ በመጠየቅ ልዩ ፍላጎቱን ገለጸ። "እርሱም፦ እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፣ እኔም አሳርፍሃለሁ አለ። እርሱም፦ አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ ፤ከዚህ አታውጣን አለ።" (ዘፀአት 33: 13-15)። በእርግጥም፣ ሙሴ የተሰጠውን ተስፋ አልተጠራጠረም ነበር፣ ነገር ግን ዳግም እንዲረጋገጥለት ፈለገ፣ ምክንያቱም በዘፀአት 23: 20-21 ጌታ ከዚህ ቀደም በሚከተሉት ቃላት ማረጋገጫ ሰጥቶት ነበር፦ "እነሆ፣ በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ፣ ወደ አዘጋጀሁልህም ስፍራ ያገባህ ዘንድ መልአክን በፊትህ እሰዳለሁ። ተጠንቀቀው፣ ድምፁንም ታዘዝ፣ አታስቆጣውም፤ መተላለፋችሁን ይቅር አይልምና፤ ስሜ በእርሱ ውስጥ ነውና።" የጌታ የግል መገለጥ ነበር።

ስለዚህ ዓይነት የሚታይ የመገለጥ ቅርጽ የሚናገሩ ሌሎች የመጸሕፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች አሉ። በኢሳይያስ 63: 9 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "በጭንቀታቸዉ ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፣ የመገኘቱ መልአክ አዳናቸው፤ በፍቅሩና በምህረቱ አዳናቸው፤ በቀደመዉም ዘመን ሁሉ አንስቶ ተሸከማቸው።" ጌታ በመልአክ ቅርጽ ተገኝቶ ነበር። እርሱ እስራኤልን ያዳነው ነው፤ እነርሱ ሲጠብቁት የነበረው እርሱ ነበር። በሚልክያስ 3: 1 ላይ እንዲህ ይላል፦ "...የምትፈልጉትም ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፣ የቃል ኪዳኑም መልእክተኛ..."

"መልአክ" እና "መልእክተኛ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ናቸው። በሐዋርያት 7: 38 ላይ ስለ ሕግ አሰጣጥ፣ ስለ ሙሴ፣ እና ከእርሱ ጋር ስለተነጋገረው መልአክ እንዲህ እናነባለን፦ "ይህ ሰዉ በሲና ተራራ ከተናገረዉ መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በነበረዉ ቤተክርስቲያን ዉስጥ የነበረው ነዉ፣ ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸዉን ቃላት የተቀበለ እርሱ ነው።" ሁላችንም እንደምናውቀው እግዚአብሔር መልአክን አልላከም፣ ነገር ግን ጌታ ራሱ ወርዶ ትእዛዛትን ለሙሴ ሰጥቷል። እርሱ በቀላሉ በመልአክ በሚታይ ቅርጽ ተገለጠ።

በብሉይ ኪዳን በሚታይ ቅርጽ መገለጡ በሰው ሥጋዊ መልክ ለግል መገለጡ በጣም አስፈላጊ ነው። ያዕቆብን እንደ ምስክር እንጥራ። ስለ እርሱ እንዲህ እናነባለን፦ "ከመልአኩም ጋር ታገለ ፤ አሸነፈዉም፤በፊቱ ሞገስን ለማግኘት አልቀሶ ለመነው። እርሱንም በቤቴልም አገኘው፣ በዚያም ከእኛ ጋር ተናጋገረ። እርሱም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ፤ ጌታ የመታሰቢያው ነው።" (ሆሴዕ 12: 4-5)። የሠራዊት ጌታ ወይም እግዚአብሔር ቢጠቀስም፣ ሁልጊዜም ራሱን በተለያዩ መንገዶች የሚገልጥ፣ ግን ለዘላለም ተመሳሳይ ሆኖ የሚኖር ያው አንድ አካል ነው።

የያዕቆብ ከጌታ ጋር የነበረው ገጠመኝ ቀደም ተብሎ በዘፍጥረት 32፣ ከቁጥር 24 ጀምሮ ተመዝግቧል፦ "ያዕቆብም ብቻውን ቀረ፤ አንድ ሰውም ከእርሱ ጋር እስከ ንጋት ድረስ ይታገለዉ ነበር... እርሱም፦ ስምህ ከእንግዲህ እስራኤል ይባል እንጅ ያቆብ አይባል፣ ከእግዚአብሔርና ከሰዉም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና... ያዕቆብም የቦታውን ስም ጵኒኤል (Peniel) ብሎ ጠራው፤ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁና ሕይወቴ ተጠብቋል ሲል።"

ይህ ተሞክሮ በቀላሉ ሊታሰብ አይችልም። ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ፣ በራሱ ግርማ የሚኖረው፣ በሁሉም ቦታ የሚገኘው፣ እንደዚህም ሆኖ ራሱን በሰው ቅርጽ ገልጦ፣ ያዕቆብም ከእርሱ ጋር ሊታገል ችሏል። ያዕቆብ ከመሞቱ በፊት፣ የዮሴፍን ልጆች ባረከ፣ እጆቹንም በመስቀል ቅርጽ አስተላልፎ እእንዲህ አለ፡- “አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እርሱ እግዚአብሔር ፤ እስከ ዛሬ ድረስ ዘመኔን ሁሉ የመገበኝ እግዚአብሔር፣ ከክፉ ሁሉ ያዳነኝ መልአክ፣ እነዚህን ብላቴኖች ባርክ...” (ዘፍጥረት 48: 15-16)።

የማይታየው እግዚአብሔር በሚታይ መልክ ሊገለጥ ይችላል። በዘፀአት 24፣ ከቁጥር 9 ጀምሮ እንዲህ እናነባለን፡- “ከዚያም ሙሴ፣ አሮን፣ ናዳብ፣ እና አቢሁ፣ እና ሰባዎቹ የእስራኤል ሽማግሌዎች ወጡ፤ የእስራኤልንም አምላክ አዩ... እግዚአብሔርንም አዩ፣ በሉና ጠጡ።”

ከሁሉን ቻይ አምላክ ፊት ማን ሊገኝ እና በፊቱ እርሱ እያለ ሊበላና ሊጠጣ እንደሚችል ማን ሊያስብ ይችላል? እኛ እውነት እንደሆነ እናምናለን፣ ምክንያቱም በቅዱስ ቃሉ ተመዝግቧል። እግዚአብሔር በክብሩ ሙላት በነበረበት ጊዜ፣ በዘላለም በመንፈስ ማንም ሊያየው አይችልም ነበር። ከመጀመሪያው ጀምሮ፣ በመንፈሳዊ አካል ራሱን ከገለጠ በኂላ ብቻ ነው የታየው። ሰባዎቹ ሽማግሌዎችና ከሙሴ ጋር የነበሩት፣ ጌታ አምላክን በክብሩ አዩ። እግዚአብሔር እውነት ነው። መናገር ይችላል፣ መስማት ይችላል፣ መጻፍ ይችላል፣ ወዘተ።

ነቢዩ ሕዝቅኤልም ከአጋጣሚዎቹ አንዱን መዝግቧል፡- “በራሳቸውም ላይ ከነበረው ጠፈር በላይ የሰንፔር ድንጋይ የሚመስል አምሳያ ነበረ፣ በዙፋኑም አምሳያ ላይ እንደ ሰው መልክ አምሳያ ነበር። ” (ሕዝቅኤል 1: 26)። በማንኛውም ጊዜ ማንም ሁለት ወይም ሦስት አካላትን በዙፋኑ ላይ አላየም። “ሦስት አካል ያለው አምላክ”፣ “ሥላሴ” የሚሉት ቃላት በመጻሕፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኙም። አንድም ነቢይ ወይም ከሐዋርያት ማንም ከእግዚአብሔር ውስጥ ከብዙ አካላት በላይ እንዳሉ የሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን ፈጽሞ አልተረጎመም። የምናገኘው የዚህን አንድ እግዚአብሔር የተለያዩ መገለጦች ብቻ ነው።

## ማብራሪያ

ለረጅም ጊዜ በተስፋፉት በተሳሳቱ ትርጓሜዎችና ጽንሰ-ሐሳቦች ምክንያት፣ እግዚአብሔር በፍጥረት ጊዜ “ሰውን በመልካችን እንፍጠር...” (ዘፍጥረት 1: 26) ሲል ለማን እንደተናገረ ማብራራት አስፈላጊ ነው። የዚህን አባባል ማብራሪያ እንፈልግም፣ ከእግዚአብሔር ቃል ራሱ ግልጽ የሆነ መልስ እንፈልጋለን። እዚህ ላይ ዓለም አቀፋዊ ፈተናው ተሰጥቷል፡- መቼና የት ነው አንድ ነቢይ ወይም ሐዋርያ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ብዙ አካላት እንዳሉ ያነበበው ወይም የገለጸው?

በኢዮብ 38፣ ከቁጥር 4-7 ጀምሮ፣ ጌታ አገልጋዩን እንዲህ ሲል ጠየቀ፡- “እኔ (እኛ አይደለም) የምድርን መሠረት ስጥል የት ነበርህ? ታስተዉል እንደ ሆንህ ተናገር፤የምታዉቅ ከሆነ ማን ነው መስፈሪያዋን የወሰነ ፤ በላይዋስ የመለኪያ ገመድ የዘረጋ ማነው. የጣለው ? ወይስ አጥቢያ ኮከቦች

በአንድነት ሲዘምሩ፣ የእግዚአብሔር ልጆችም ሁሉ በደስታ ሲጮሁ ፤ መሰረቶችዋ በምን ላይ ተተክለዉ ነበር? የማዕዘን ድንጋዩን ያቆመ ማን ነዉ?" ይህን ሁሉም ይረዳል። እግዚአብሔር ምድርን በፈጠረ ጊዜ፣ ሁሉም የሰማይ ሠራዊት ተገኝተው በደስታ ጮኹ። እግዚአብሔር ብቻውን አልነበረም፣ ወይም ከአንድ አካል በላይ ሆኖ አልነበረም። እርሱ በእርግጥ ለራሱ ወይም ለሌላ አምላክ አልተናገረም፣ ሌላ አምላክ የለምና። እርሱ ከእርሱ ጋር ለነበሩት የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ለተጠሩት መላእክት ተናገረ።

በዘፍጥረት 11: 7 ላይ፣ ጌታ እንደገና በብዙ ቁጥር እንዲህ ሲል ተናገረ፦ "ኑ፣ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማዉ ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀዉ።" እንደገና ጌታ በዙሪያው ለነበሩት ተናገረ።ቁጥር 5 በግልጽ እንዲህ ይላል፦ "ጌታም ከተማዋን ሊያይ ወረደ..." ደግሞም እንደገና በሰማያዊ ሠራዊት ተከቦ ታይቷል። ነቢዩ ሚክያስ በጣም አስደናቂ ምስክርነት ይሰጣል። እንዲህ ሲል ገለጸ፦ "ጌታን በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁ፣ የሰማይም ሠራዊት ሁሉ በቀኝና በግራው ቆመው ነበር።" (2ኛ ዜና መዋዕል 18: 18)። በዚህ ሁኔታ ውስጥም ጌታ ለማን እንደተናገረ በጣም ግልጽ ነው። ከእርሱ ጋር በፊቱ ለቆሙት ሰማያዊ ፍጥረታት ብቻ ሊናገር ችሏል።

ነቢዩ ኢሳይያስ ከተፈጥሮ በላይ ከሆኑት ገጠመኞቹ አንዱን መዝግቧል፦ "ጌታን በዙፋን ላይ ከፍ ብሎና  ተቀምጦ አየሁ፣ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶ ነበር። ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመዉ ነበር... አንዱም ለአንዱ ፦ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድርም ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች አለ።" (ኢሳይያስ 6: 1-3)። እንደነዚህ ያሉ ዘገባዎች ተጨማሪ ማብራሪያ አያስፈልጋቸውም። በጣም የሚያበሩ ናቸው። በሰው ቅርጽ ባሉ መላእክት እና በኪሩቤልና በሱራፌል መካከል ያለውን ልዩነትም እናያለን። እነዚህ ክንፎች ያላቸው ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ፍጥረታት ናቸው፣ ሁልጊዜ ጌታን የሚያመሰግኑ። መላእክት በፊቱ ይቆማሉ፤ እነርሱ የሚያገለግሉ መንፈሶች ናቸው (ዕብራውያን 1: 14)። በኢሳይያስ 6: 8 ላይ "ማንን እልካለሁ፣ ማንስ ይሄድልናል?" ብሎ ያናገራቸዉ እነርሱን ነበር። "እኛ" የሚለው ቃል ከአምላክ ውስጥ ከሌላ አካላት ጋር ፈጽሞ አልተገናኘም። ይህ ፈጽሞ የማይቻል ነው፤ እግዚአብሔር በሦስት አካላት እንዳለ ማሰብ እንኳ ክብሩን ከመስደብ አይተናነስም። እርሱ ሦስት አካላት ሳይሆን አንድ ነው፣ እንዲሁም ሦስት ራስ ያለው አንድ አካል አይደለም። ዘመናዊ የነገረ መለኮት ምሁራን እንደሚሉትም "ኢኮኖሚያዊ ሥላሴ" አይደለም።

እግዚአብሔር በእርሱ ላመኑት ራሱን ገለጠ። ተስፋዎቹን ተቀበሉ እና ስለ እርሱ በጨለማ ውስጥ አልቀሩም። በብሉይ ኪዳን ያሉ ነቢያትም ሆኑ በአዲስ ኪዳን ያሉ ሐዋርያት፣ ከእነርሱ መካከል አንዳቸውም ቢሆኑ ስለ እግዚአብሔር ተከራክረው አያውቁም። ይህ የጀመረው ከክርስቶስ በኋላ በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር፣ የግሪክ ፍልስፍናዎች እና የሮማውያን ስለ አማልክቶቻቸው የነበሩ ሀሳቦች ወደ ተሳሳተዉ ክርስትና ሲገቡ።  "ሊቃውንት" የሚባሉት አምላክን እንደ ባህላዊ አስተሳሰባቸው መሠረት ለማብራራት ሞክረዋል። የሥላሴ አስተምህሮ የመጣው በዚህ መንገድ

ነው። አሳዛኝ ግን እውነት ነው፣ በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ያለው ሥነ-መለኮት በሰዎች አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው፣ እና እንደ አጠቃላይ የሚታመነው፣ በነቢያትና በሐዋርያት የመጀመሪያ ምስክርነት ላይ አይደለም። ስለ አምላክ የተሳሳተው ትምህርት በተለምዶ እንደ ትክክለኛ ትምህርት ተቀባይነት አግኝቷል፣ ስለእግዚአብሔርም እውነተኛዉ እውቀት እንደ ተሳሳተ ተቆጠሯል። እግዚአብሔር እኛ ለመሥራት እንደምንሞክረው አይደለም፣ እርሱ በቀላሉ እንዳለዉ ነው። ሰዎች አማልክትን ይሠራሉ፣ ጌታ ግን አምላክ ሆኖ ይኖራል፣ ትናንት፣ ዛሬና ለዘላለም ተመሳሳይ ነው (መዝሙር 102: 27፤ ኢሳይያስ 48: 12፤ ዕብራውያን 13: 8)።

እግዚአብሔር ራሱን አላበዛም፣ አልተለወጠም። ማንም እውነተኛ አይሁዳዊ የሥላሴን ሀሳብ ፈጽሞ ሊቀበል አይችልም። ይህ ፈጽሞ የማይቻል ነው፣ ምክንያቱም እንዲህ ያለ ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የለም። እግዚአብሔር በትልቅ ዕቅዱ መሠረት ራሱን በተለያዩ መንገዶች ብቻ ይገልጣል።

## ድልድዩ

አምላክን በተመለከተ ሰዎች አዲስ ኪዳንን ከብሉይ ኪዳን የበለጠ ተሳስተው ይረዱታል። ይህ በቀላሉ እስከ ዛሬ ድረስ በወረስናቸው የስነ-መለኮት ትምህርቶች የመጣ ውጤት ነው። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ናቸው። በኒቂያ ጉባኤ (325 ዓ.ም.) እንኳ ስለ አምላክ ምንም ውይይት አልነበረም። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ዋናው ክርክር የነበረዉ በኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነት ዙሪያ እንደሆነ ያውቃል። አትናቴዎስ ክርስቶስ ፍጡር ነው ብሎ ያስተማረውን አርዮስን በመቃወም ይከራከር ነበር። ስለ ሥላሴ የቀረቡት ቀመሮች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው የተጀመሩት። እነርሱም የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ውጤት ናቸው – ፍጹም የተሳሳተ የቅዱሳት መጻህፍት ግንዛቤ። የነቢያትና የሐዋርያት ቃላት ግምት ውስጥ አልገቡም። ይህ ትምህርት የመጣው ከዚያ ፍልስፍናዊ፣ ነገረ መለኮታዊ አስተሳሰብ ነው። ሰዎች ራሳቸውን ሦስት አካላት አንድ አምላክ ናቸው ብለው እንዲያምኑ ለማዘዝ ሞክረዋል። ነገር ግን አንድን አላዩም፣ ሦስት አዩ። ከአሀዳዊነት ወደ ሦስትነት መዞርም ተጠናቀቀ። እነርሱ አንድን የሚሠሩ ሦስት አይደሉም – እርሱ አንድ ነው፣ ራሱን እንደ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የገለጠዉ። እግዚአብሔር ከእኛ በላይ፣ ከእኛ ጋር፣ እና በእኛ ውስጥ።

የእግዚአብሔርን ታላቅ የማዳን ዕቅድ ስንመለከት፣ አንድ አምላክ መሥራት እንደጀመረ እናውቃለን። በዘላለም ዉስጥ እርሱ በምንም መንገድ ራሱን አልገለጠም ነበር። ነገር ግን በመጀመሪያ እንደ “ሎጎስ” – ቃል፣ የእግዚአብሔር የሚሠራ ክፍል – ተገለጠ። ከዚያም በሥጋ አካል ራሱን ገለጠ (ዮሐንስ 1: 1)። እግዚአብሔር በነቢያት አማካኝነት ተናገረ፣ ነገር ግን በወልድ መናገሩ ከእንግዲህ ትንቢት አልነበረም፣ መልስ፣ ውጤቱ ራሱ ነበር። የምንመለከተው የእግዚአብሔርን ታላቅ መገለጥ ነው። ከዘላለም የነበረው፣ ወደ ጊዜ ገባና ታሪክ ሠራ። በመጀመሪያ የነበረው ቃል ሥጋ ሆነ፣

በእኛም መካከል አደረ (ዮሐንስ 1: 14)። ብርሃን ወጣ፣ አዲስ ቀን ነጋ – የመዳን ቀን (ኢሳይያስ 49: 8)። ፀሐይ በክንፎቿ ጽድቅ ይዛ ወጣች። አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ወጣ።

እግዚአብሔር ዕቅዱን በሰው ልጆች ውስጥ መፈጸም ጀመረ። እርሱና መገለጡ ተመሳሳይ እንደሆኑ ማየት አለብን፣ የተለያዩ መገለጦች ቢኖርም እንኳ። እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደነበረ ብቻ ነው እውነት የሆነው ወይስ ራሱን ከእኛ ጋር አስታርቆአል (2ኛ ቆሮንቶስ 5: 19) የሚለውም እውነት ሊሆን ይችላል? ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍት አንዱ አትናቴዎስ የሰጠውን መግለጫ ጠቅሷል፣ እንደገና እሱ ኢሬኔዎስን ጠቅሷል። ታሪክ ጸሐፊው እነዚህን ቃላት ጻፈ፦ "ለአትናቴዎስ ወሳኙ ሀሳብ በኢየሱስ እግዚአብሔር ራሱ ለእኛ መገለጡ ነበር፤ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ አሳወቀንና አዳነን፤ በእርሱም አብ ራሱ አለን።"

ማርቲን ሉተር እንዲህ አለ፦ "አዳኙ ራሱ እግዚአብሔር መሆን አለበት፣ ምክንያቱም ማንም ሌላ ከአስከፊው ውድቀት ከኃጢአትና ከዘላለም ሞት ሊያድነን አይችልም ነበር። ኃጢአትንና ሞትን አስወግዶ ጽድቅንና የዘላለም ሕይወትን የሚያመጣ የዘላለም አካል ካልሆነ በቀር ሌላ ሊያድነን የሚችል መንገድ አልነበረም። ይህ መልአክ ወይም ሌላ ፍጡር ሊሆን አይችልም ነበር፣ ራሱ እግዚአብሔር መሆን ነበረበት።" ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነው የሥላሴ ትምህርት ለአይሁዶች፣ ለሙስሊሞችና ለሌሎች ሁሉ ትልቁ መሰናክል ሆነ። የእግዚአብሔርን መገለጥ እንደ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በተከታታይ ቅደም ተከተል ከመመልከት ይልቅ፣ የሰው አእምሮ ሦስት አካላት አድርጎ፣ እርስ በርስ ተቀምጠው አቅርቧቸዋል።

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ሁሉ ብሉይና አዲስ ኪዳን ሙሉ በሙሉ መስማማት አለባቸው ብሎ ማመን አለበት። አንድም እርስ በእርሱ የሚጋጭ ሊኖር አይችልም። ትንቢትና ፍጻሜው መመሳሰል አለባቸው፣ እናም ይመሳሰላሉ! ብሉይ ኪዳን እርሱ እንደሚመጣ ይናገራል፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ ወደ ሰው ቅርጽ እንደገባ ያረጋግጣል።

በዘፍጥረት 1: 26-28 መሠረት፣ አዳም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሲሆን ይህም በመንፈሳዊ አካል ነበር። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ገና ሥጋ ለብሶ አልታየም ነበር። በኋላ፣ በዘፍጥረት 2: 7 ላይ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር ሠራው። ከዚያ በኋላ፣ ሔዋን ከአዳም ተወስዳ ወጣች። ሰው በሥጋዊ አካል ውስጥ ስለወደቀ፣ እግዚአብሔር እኛን ሊያድነን እንዲችል ወደ ተመሳሳይ አካል መውረድ ነበረበት። ክርስቶስ ሁለተኛው አዳም ነበር። በቀራኒዮ ጎኑ ተከፈተ፣ በደሙም ሙሽራው ተገለጠች፣ ተዋጀች። እርሷም ከሥጋው ሥጋ፣ ከአጥንቱም አጥንት ናት (ኤፌሶን 5: 30)። እኛ እንደ ሰው ልጆች ወደ መለኮታዊ ሥርዓት መመለስ ነበረብን። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በሥጋ ወደ እኛ መምጣት ነበረበት። ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ፡ እርሱ በመንፈስ አምላክ ነዉ ። በሰማይ እንደ አባት፣ በምድርም እንደ ወልድ ነበር። ሰማይንና ምድርን፣ እግዚአብሔርንና ሰውን ለማገናኘት ይህ የግድ መሆን ነበረበት።

አዲስ ኪዳን አንድ አምላክ እንዳለ ይመሰክራል፣ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን። እንደ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ መገለጡ ያን አንድ አምላክ አላበዛውም። "ኢየሱስም መለሰለት፡- ከሁሉም ትእዛዛት የመጀመሪያው፡- ስማ፣ እስራኤል ሆይ፡- ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ አምላክህን ጌታን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም አእምሮህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ፤ ይህ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው።" (ማርቆስ 12: 29-30)። ጌታ የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን ነገር ይናገራል ብሎ ማንም እንዴት ሊታሰብ ይችላል! ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 3: 30 ላይ እንዲህ ሲል ይመሰክራል፡- "አንድ አምላክ ስለሆነ፣ መገረዝን በእምነት የሚያጸድቅ፣ ያልተገረዘንም በእምነት ነው።" ይሁዳ የጻፈውም በጣም ግልጽ መግለጫ ነው፡- "ብቸኛ ለሆነው ጥበበኛ አምላክ፣ አዳኛችን፣ ክብርና ግርማ፣ ግዛትና ኃይል፣ አሁንም ለዘላለምም ይሁን። አሜን።" (ቁጥር 25)።

ወደተለያዩ መገለጦች ከመግባታችን በፊት፣ በአዲስ ኪዳን ላይ አጽንዖት እንደተሰጠው፣ በአምላክነቱ ላይ በድጋሚ ማተኮር እንወዳለን። በሮሜ 9: 4-5 ላይ፣ ሐዋርያው እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "...እስራኤላውያን ናቸዉና ፤ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርአት የተስፋዉም ቃላት ለእነርሱ ናቸዉና፤ አባቶችም ለእነርሱ ናቸዉና ፣ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፣ እርሱም ከሁሉም ላይ የሆነ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነዉ፤ አሜን።" እንዲህ ያለውን መግለጫ ማን ሊክድ ይችላል! ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ሲል ገለጸው፡- "የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ እና እውነተኛም የሆነዉን እናውቅ ዘንድ ማስተዋልን እንደሰጠን እናውቃለን፤ እዉነተኛ በሆነዉ በእርሱ አለን ፣ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።" (1ኛ ዮሐንስ 5: 20)።

እግዚአብሔር ራሱን እንደ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ መግለጥ ይችላል፣ እናም ያው አንድ አምላክ ሆኖ ይኖራል። ጳውሎስ አስደናቂ ምስክርነት ይሰጣል፡- " እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነዉ ፡- እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠ፣ በመንፈስ የጸደቀ፣ በመላእክት የታየ፣ በአሕዛብ መካከል የተሰበከ፣ በዓለም የታመነ፣ በክብር ያረገ።" (1ኛ ጢሞቴዎስ 3: 16)። የነቢያትና የሐዋርያት ምስክርነት በሚያምኑት ሁሉ ሊሰማና ተቀባይነት ሊኖረዉ ይገባል። የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነት ለእምነታችን ፍጹም መሠረት ነው። በቆላስይስ 2: 2 ላይ፣ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "ልቦቻቸው እንዲጽናኑ፣ በፍቅር አንድ ሆነው፣ የእግዚአብሔርን፣ የአብንና የክርስቶስን ምሥጢር በማወቅ እስከ ሙሉ የማስተዋል ብልጥግና ድረስ እንዲደርሱ፣ በእርሱም የጥበብና የእውቀት ሀብት ሁሉ የተሰወረ ነው።" የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ መገለጥ ስንቀበል ብቻ ነው እነዚህን የተሰወሩ ሀብቶች ሁሉ የምናገኘው።

## ፈጣሪ

በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር የተሰጡት ነገሮች በአዲስ ኪዳንም ለጌታ ለኢየሱስ ተሰጥተዋል። በሁለቱም ውስጥ ስለ አዳኝ፣ ስለ ንጉሥ፣ ስለ እረኛ፣ ስለ ፈራጅ ወዘተ እናነባለን። እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደሆነ እናውቃለን። ለፍጥረት አንድ አካል ብቻ ተጠያቂ መሆኑም ግልጽ መሆን አለበት።

በዮሐንስ 1: 10 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "...በዓለም ነበር፣ ዓለሙም በእርሱ ሆነ ፤ ዓለሙም አላወቀውም።" ይህ መግለጫ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል። በቆላስይስ 1: 16-17 ያለውም ለእርሱ ይሠራል፦ "በሰማይና በምድር ያሉ ሁሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋኖችም ቢሆኑ፣ ሥልጣናትም ቢሆኑ፣ አለቅነትም ቢሆኑ ወይም ገዥዎች – ሁሉም ነገር በእርሱ ተፈጠረ፣ ለእርሱም ተፈጠረ፤ እርሱም ከሁሉም ነገር በፊት ነው፣ ሁሉም ነገርም በእርሱ ጸንቶ ይኖራል።" እንዲህ ያሉ መግለጫዎችን ከፍጥረት ጋር በተያያዙ ሌሎች ዘገባዎች ሁሉ ጋር ማስታረቅ እንችላለን?

በ1ኛ ቆሮንቶስ 8: 6 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፣ ነገርም ሁሉ በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን ።" እዚህ ሁለት ነገሮች ጎልተው ታይተዋል፦ በመጀመሪያ፣ አንድ አምላክ፣ አብ እንዳለ፣ እና ሁሉም ነገር በእርሱ እንደተሠራ ተነግሮናል፤ ከዚያም አንድ ጌታ ብቻ አለ፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ እና ሁሉም ነገር በእርሱ ተሠራ ይላል። የፍጥረት ሥራ የተከናወነው በማን ነው? ሁለት ፈጣሪዎች አሉን? በእርግጥ የሉም። አንድ ብቻ ነው። እርሱ እግዚአብሔር ነው፣ እንደ አብም በወልድ ተገለጠ። ወልድም ጌታ ነው፣ እንደ ጌታም እርሱ እግዚአብሔር ነው።

በአዲስ ኪዳን ትንቢታዊ መጽሐፍ ውስጥ በምዕራፍ 4: 11 ላይ ስለ ጌታ አምላክ እንደገና እናነባለን፦ "ክብርንና ኃይልን ለመቀበል ይገባሃል፣ ጌታ ሆይ፤ ሁሉንም ነገር ፈጥረሃልና፣ በፈቃድህም የሆኑና የተፈጠሩ ናቸውና።" ግልጽ የሆነ ምስል ለማግኘት ለአንድ ርዕሰ ጉዳይ የተለያየ ማጣቀሻዎችን መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን እናያለን።

## እኔ ነኝ

በዮሐንስ 8: 24 ላይ፣ ጌታችን እንዲህ ሲል መሰከረ፦ "እንግዲህ፦ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ ብዬ ነገርኋችሁ፤ እኔ እርሱ መሆኔን ካላመናችሁ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና።" "እኔ ነኝ" ያዳነን መሆኑን ካላመንን፣ በኃጢአታችን እንሞታለን። በሙሴ ዘመን እንኳ "እኔ ነኝ" ተናግሯል። "ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፦ እነሆ፣ ወደ እስራኤል ልጆች ስመጣ፣ የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ልኮኛል ብዬ እላቸዋለሁ፤ እነርሱም፦ ስሙ ማን ነው? ብለው ቢሉኝ፣ ምን እላቸዋለሁ? እግዚአብሔርም ሙሴን፦ "ያለ እና የሚኖር" እኔ ነኝ አለ። ደግሞም፦ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በል፦ እኔ ነኝ ወደ እናንተ ልኮኛል አለ።" (ዘፀአት 3: 13-14)።

ጌታችን በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበረውን ተመሳሳይ አባባል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሟል። እርሱም፦ "እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ። እኔ ትንሣኤ ነኝ። እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ወዘተ አለ። በዮሐንስ 8: 57-58 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "አይሁድም፦ ገና አምሳ ዓመትህ አልሆነህም፣ አብርሃምን አይተሀዋልን? አሉት። ኢየሱስም፦

እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።" "እኔ ነኝ" ለአብርሃምና ለሙሴ የተናገረው ያው ጌታ ነበር።

በኢሳይያስ 44: 6 ለ፣ ጌታ እንዲህ አለ፡- "እኔ የመጀመሪያው ነኝ፣ እኔም የመጨረሻው ነኝ፣ ከእኔ በቀር አምላክ የለም።" ተመሳሳይ አባባል በኢሳይያስ 48: 12 ለ ላይ ይገኛል፡- "እኔ እርሱ ነኝ፤ እኔ የመጀመሪያው ነኝ፣ እኔም የመጨረሻው ነኝ።" በብሉይ ኪዳን፣ ጌታ እግዚአብሔር ራሱን የመጀመሪያውና የመጨረሻው እንደሆነ፣ ከእርሱ በቀርም አምላክ እንደሌለ ይናገር ነበር። በአዲስ ኪዳን፣ ጌታችን በራእይ 1: 17-18 ላይ እንዲህ አለ፡- "አትፍራ፤ እኔ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነኝ፤ ሕያው የሆንኩ እኔ ነኝ፣ ሞቼም ነበር፤ እነሆም፣ ለዘላለም ሕያው ነኝ።"

በብሉይ ኪዳን፣ ጌታ አምላክ – ያህዌ – "እኔ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነኝ" አለ፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታ ኢየሱስ "እኔ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነኝ" ይላል። ሁለት የተለያዩ አካላት ከሆኑ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው በትክክል ማን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልገናል። በራእይ 1: 8 ላይ፣ በሚያምር ሁኔታ እንዲህ ተጣምሮ ተቀምጧል፡- "አልፋና ዖሜጋ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ፣ ይላል ጌታ፣ ያለውና የነበረውና የሚመጣው፣ ሁሉን ቻይ።" ጌታ ኢየሱስ ራሱን ሁሉን ቻይ እንደሆነ መጥራቱ በጣም የሚገርም ነው። አይ፣ ግን ሌላ ቢሆን ኖሮ ይገርም ነበር! በቃሉ ውስጥ በትክክል መንገዝ እና ነገሮች በመንፈስ ቅዱስ መገለጣቸው ድንቅ ነው። የብሉይ ኪዳን ያህዌ የአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ነው። እርሱ ለዘላለም አይለወጥም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን የእርሱን ምስክርነት ማመን አለብን። እግዚአብሔር ፈጽሞ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ አያስጽፍም። እርሱ ሁልጊዜ የተናገረውን ዛሬም ይናገራል። ራሱን ፈጽሞ ማረም አያስፈልገውም። እኛ ነን እርማት የሚያስፈልገን።

### ንጉሡ

እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ በብሉይ ኪዳን ጌታ አምላክ ንጉሥ ተብሎ እንደተጠቀሰ ያውቃል። ዳዊት እንዲህ ሲል ጸለየ፡- "የጩኸቴን ድምፅ ስማኝ፣ ንጉሤና አምላኬ ሆይ፤ ወደ አንተ እጸልያለሁና።" (መዝሙር 5: 2)። ነቢዩ ኤርምያስ እንዲህ አለ፡- "ጌታ ግን እውነተኛ አምላክ ነው፣ ሕያው አምላክም፣ የዘላለም ንጉሥም ነው።" (ምዕራፍ 10: 10)። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ገለጸው፡- "እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ አዳኙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። " (ምዕራፍ 44: 6)።

በዘካርያስ 9: 9 ላይ፣ ስለአዳኙ የተስፋውን ቃል እናገኛለን፡- " አንች የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እጅግ ደስ ይበለሽ ፤እልል በይ፣ እነሆ፣ ንጉሥሽ ጻድቅ እና አዳኝ ነዉ ፤ ትሁትም ሆኖ በአህያም፤ በአህያቱ ግልገል በዉርንጭላይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል።" በአዲስ ኪዳን፣ የዚህ ትንቢት ፍጻሜ በማቴዎስ 21: 1-4 ላይ ይገኛል። ሕዝቡ ንጉሣቸው ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እየገባ መሆኑን

ተገነዘቡ:: ልባቸው በደስታ ሞልቶ ነበር፣ መንገዱን በማስጌጥና በመጮህ በተግባር ለመግለጽ ሞከሩ:: "ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ! በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው! ሆሣዕና በአርያም!"

አዳኙ በተወለደ ጊዜ፣ ጠቢባን ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም መጡ እንዲህ ሲሉ ጠየቁ፡- "የተወለደዉ የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?" (ማቴዎስ 2: 2):: ጌታችን በጲላጦስ ፊት በቆመ ጊዜ፣ "የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?" ተብሎ ተጠየቀ (ዮሐንስ 18: 33):: ጲላጦስ እንደገና፡- "እንግዲያውስ አንተ ንጉሥ ነህን? ኢየሱስም መለሰ፡- እኔ ንጉሥ እንደሆነሁ አንተ ትላለህ:: እኔ ለእዉነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጄአለሁ ስዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፣ ስለ እውነት እንድመሰክር ፤ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለዉ::" (ቁጥር 37)::

በብሉይ ኪዳን ጌታ እግዚአብሔር ንጉሥ ተብሎ እንደተጠራው ሁሉ፣ በአዲስ ኪዳንም ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥ ተብሎ ይጠራል:: ጳውሎስ በሚያምር ሁኔታ እነዚህን ቃላት ጠቅልሎ ገለጸ፡- "ብቻዉን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋዉ ለማይታየዉም ለዘመናት ንጉስ ምስጋናና ክብር አስከዘላለም ይሁን ፤ አሜን ::" (1ኛ ጢሞቴዎስ 1: 17):: ኦህ፣ የእግዚአብሔር ጥበብና እውቀት ምን ያህል ጥልቅ ነው! ግን አሁንም ነገሩ የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ከማስቀመጥ በላይ ይወስዳል :: እግዚአብሔርን ለማወቅ መለኮታዊ መገለጥ ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ እንደገለጠ ማመን ለእኛ አስፈላጊ ነው:: እንደዚህ ባለ ሁኔታ ብቻ ነው ሁሉንም የመጻሕፍ ቅዱስ ጥቅሶች በትክክለኛ አውዳቸው ልንገነዘብ የምንችለው::

የተነገረው መንግሥት በቅርቡ በምድር ላይ ይመጣል:: በትንቢታዊው ቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ተነግሯል:: በመዝሙር 47: 6-8 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "ለእግዚአብሔር ዘምሩ፣ ዘምሩ፤ ለንጉሣችን ዘምሩ፣ ዘምሩ:: እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና፤ በአእምሮ ዘምሩ:: እግዚአብሔር በህዝቦች ላይ ሁሉ ይነግሣል፤ እግዚአብሔር በቅድስናው ዙፋን ይቀመጣል::" እግዚአብሔር ታላቅ ንጉሥ ነው፣ መንግሥቱም በምድር ሁሉ ላይ ይሆናል:: መዝሙር 96: 9-10 እንዲህ ይላል፡- "በቅድስናዉ ስፍራ ለጌታ ስገዱለት፤ ምድር ሁሉ በፊቱ ትነዋወጥ:: በሕዝቦች መካከል ጌታ ይነግሣል በሉ:: ዓለምም እንዳይናወጥ እርሱ አጸናዉ፤ ሕዝቦችንም በጽድቅ ይፈርዳል:: " መላው ፍጥረት ያንን ታላቅ ጊዜ እየጠበቀ ነው::

በራእይ 11: 17 ላይ፣ አዋጁ ተነግሯል፡- "እንዲህ አሉ ፡- ያለህ እና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፤ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለነገስህም እናመሰግንሃለን::" ንጉሡ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እንደሆነ፣ እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ሲነገር እናያለን፣ እናም አንድ ንጉሥና አንድ መንግሥት ብቻ እንዳለ እናውቃለን:: በማቴዎስ 25: 31-32 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "የሰው ልጅ በክብሩ ሲመጣ፣ ቅዱሳን መላእክትም ሁሉ ከእርሱ ጋር፣ ያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ላይ ይቀመጣል:: በፊቱም አሕዛብ ሁሉ ይሰበሰባሉ::" እንደገና በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠው ማን እንደሆነ ልንጠይቅ እንችላለን:: በዘካርያስ 14: 9 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ጌታም በምድር ሁሉ ላይ ንጉሥ ይሆናል፤ በዚያም ቀን አንድ ጌታ ይሆናል፣ ስሙም አንድ ይሆናል::" በዚህ ግንኙነት ውስጥ

በራእይ 15: 3 ላይ የሚገኘው አዋጅም ይገባናል፦ “ታላቅና ድንቅ ናቸው ሥራዎችህ፣ ጌታ አምላክ ሁሉን ቻይ፤ ጻድቅና እውነተኛ ናቸው መንገዶችህ፣ የቅዱሳን ንጉሥ።” በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎችን መስጠት እንችላለን። ሁለቱም፣ ጌታ እግዚአብሔር እና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ንጉሥ ተብለው ተጠርተዋል። የብሉይ ኪዳን ያህዌ የአዲስ ኪዳን ኢየሱስ መሆኑ እውነት ካልሆነ፣ እግዚአብሔር ጌታ መሆኑ እውነት ካልሆነ፣ ያን ጊዜ ሁለት የተለያዩ ነገሥታት ይኖሩናል። ያ በእርግጥ የማይቻል ነው።

## ዳኛው

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር ዳኛ መሆኑን ይመሰክራሉ፤ በተመሳሳይ መልኩ ጌታም ዳኛ ተብሎ እንደተጠቀሰ እናገኛለን። መዝሙር 50: 6 እንዲህ ይላል፦ “…እግዚአብሔር ራሱ ዳኛ ነውና”፣ መዝሙር 58: 11፣ “…በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ።” ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕራፍ 33: 22 ላይ እንዲህ ሲል ጻፈ፦ “ጌታ ዳኛችን ነው፣ ጌታ ሕግ ሰጪያችን ነው፣ ጌታ ንጉሣችን ነው፤ እርሱ ያድነናል።” ሕጉን የሰጠው እርሱ ራሱ እንደ ሕጉ ይፈርዳል። በአዲስ ኪዳን ያዕቆብ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፦ “አንድ ሕግ ሰጪ አለ፣ እርሱም ሊያድንና ሊያጠፋ የሚችል ነው።” (ምዕራፍ 4: 12)። ነቢዩ ኤርምያስም ጌታን እንደ ዳኛ ይናገራል፦ “አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ፣ በጽድቅ የምትፈርድ…” (ምዕራፍ 11: 20)። በሕይወቱ መጨረሻ ላይ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ቻለ፦ “ከእንግዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ያም ጌታ፣ ጻድቁ ዳኛ፣ በዚያ ቀን ይሰጠኛል።” (2ኛ ጢሞቴዎስ 4: 8)። በዮሐንስ 5: 22 ላይ እንዲህ ይላል፦ “አብ ማንንም አይፈርድምና፣ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጥቶታልና።”

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ላይ፣ ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት ሲሰብክ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያዋንና የሙታን ዳኛ እንደሆነ ገለጸ። ይህንን ከዕብራውያን 12: 23 ጋር አወዳድሩ፣ እግዚአብሔር ዳኛ ተብሎ በተጠቀሰበት፦ “…ለሁሉም ዳኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር…”። እንደገና፣ እንግዲያውስ ዳኛው ማን ይሆናል ብሎ መጠየቅ ይቻላል። በእርግጥም፣ አንድ ሕግ ሰጪ ብቻ እንደነበረው ሁሉ፣ አንድ ዳኛ ብቻ ይሆናል። ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ጌታ፣ ስለ አብ ወይም ስለ ወልድ ብናነብ ምንም ልዩነት የለውም። ሁልጊዜም ያው አንድ አካል ማለት ነው። በተለያዩ መገለጦች የምናየው አንድ አምላክ ብቻ እንደሆነ ለዘላለም መረዳት አለብን።

## መቋረጥ

በጣም አሳዛኝ ግን እውነት ነው፣ የሰው ልጅ እግዚአብሔርንና ዕቅዱን የሚፈጽምበትን መንገድ ሊረዳ አልቻለም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለዘላለም የሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንዲኖሩት ዓላማው ነበር። ሰው ከመጀመሪያው ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንዲኖረውና ለዘላለም እንዲኖር ተወስኖ ነበር። አዳም ነፃ ፈቃድ ያለው የተፈጠረ ድንቅ ሥራ ነበር። ለእርሱ በምድር ላይ ባለው ነገር ሁሉ ላይ ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። እርሱ በእርግጥ አውቶማቲክ መሣሪያ አልነበረም።

እኛ መሰማት፣ መውደድ፣ መወሰን ወዘተ እንችላለን፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ህብረት ለማድረግ መታዘዝ ያስፈልግ ነበር። ሰው ምድርን ሊገዛ ነበር፣ ነገር ግን ሁሉን ቻይ ስሆነው ጌታ ራሱን ማስገዛት ነበረበት። ከዚያም ውሳኔ መደረግ የነበረበት ቅጽበት መጣ፣ ጌታም በቀላሉ ሊጠበቅ የሚችል ትእዛዝ ሰጠ (ዘፍጥረት 2: 17)። አዳምና ሔዋን የጌታን ቃል ይታዘዙ ነበር ብለን እናምናለን። ሆኖም ግን የሰው ልጅ አንድ ነገር ለመሞከር እና ውጤቱን ለማየት ያለውን ዝንባሌ ያሳያል፣ በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ህብረት አጡ። በፈጣሪና በፍጥረት መካከል የነበረውስምምነት ተበላሸ፣ መለያየትም ተከሰተ።

አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ባልተረበሸ ህብረት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደኖሩ አልተነገረንም። ከውድቀት በፊት ኃጢአት፣ ሕመም፣ ሥቃይ፣ እንባ፣ ሞት አልነበረም። እኛ ዘላለም እንድንኖር የተወሰንን ስለሆንን፣ እግዚአብሔር ወደ ቀድሞ ሁኔታችን የምንመለስበትን መንገድ አደረገ።

በእግዚአብሔር ላይ መጀመሪያ የተነሳው መልአካዊው ፍጥረት ሉሲፈር ተብሎ ይጠራ ነበር። በኢሳይያስ 14: 12 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ ፤እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብን ያዋረድህ አንተ ሆይ ፣ እንዴት እስከ ምድር ተቆረጥህ!" በሕዝቅኤል 28 ከቁጥር 13 ጀምሮ ያው ፍጥረት እንዲህ ተብሎ ተገልጿል፡- "በኤደን፣ በእግዚአብሔር ገነት ነበርህ…"፣ "አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ…"፣ "ከተፈጠርህበት ቀን ጀምሮ በሁሉም መንገዶችህ ፍጹም ነበርክ፣ በውስጥህ ክፋት እስኪገኝ ድረስ።"

ይህ ፍጥረት የእግዚአብሔር ዋነኛ ጠላት ነው። እግዚአብሔር በሰጠው ቦታ አልረካም ነበር፣ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ፈለገ። ከእግዚአብሔር ከተለየ ጀምሮ፣ ብቸኛው ዓላማው የሰው ልጅንም ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ሰይጣን መንፈሳዊ ፍጥረት ስለሆነ፣ ወደ እባቡ ሳይገባ የሰው ዘርን ሊያታልል አይችልም ነበር። በዚያን ጊዜ ይህ ዝርያ ከርግማኑ በኋላ እንደሆነው ተሳቢ እንስሳ አልነበረም (ዘፍጥረት 3: 14)። በዘፍጥረት 3 መሠረት እባቡ ከሔዋን ጋር ዝርዝር ውይይት ማድረግ ችሏል። ሔዋን ሁልጊዜ የጥያቄ ምልክት ወዳላቸው ክርክሮች ተሳበች። እግዚአብሔር የተናገረውን ማለቱ ነበር፣ ማለቱ ያዉ የተናገረዉን ነበር። ነገር ግን እባቡ፡- "ፈጽሞ አትሞቱም" ብሎ ተከራከረ። ሔዋን የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር ጀመረች። ሰይጣን ከእያንዳንዳችን ጋር የሚጀምረው በዚህ መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል መጠራጠር በእርግጥ ቀጥተኛ የክፉ አነሳሽነት ነው።

እግዚአብሔር ለአዳም ታላቅ ማስጠንቀቂያ ሰጠ፡- "ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህና።" (ዘፍጥረት 2: 17)። ሰይጣን በእባቡ አማካኝነት ለሔዋን በትክክል ተቃራኒውን ተናገረ፡- "ፈጽሞ አትሞቱም።" (ዘፍጥረት 3: 4)። አሁን ምንና ማን መታመን እንዳለበት ውሳኔ መደረግ ነበረበት። ሔዋን ሽባ ተደረገች፣ ከዚያም ተታለለች።

ከዚያ በኋላ፣ አዳምንም ወደ መተላለፉ ጎተተችው፣ እናም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ህብረት ተበላሸ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ መላው የሰው ዘር ከእግዚአብሔር ተለይቶ በሰይጣን ተጽዕኖ ሥር ነው። በዚህ ዓለም የተወለደ ሁሉ የሞት ልጅ ነው። በሕይወት ውስጥ እንደ ሞት በእርግጠኝነት ያለ ነገር የለም።

ከመተላለፉ በኋላ፣ ጌታ አዳምንና ሔዋንን ከገነት ማባረር ነበረበት፣ በዚህም ከሕይወት ዛፍ እንዳይበሉና በኃጢአት ውስጥ ለዘላለም እንዳይኖሩ። የዘላለምን ሕይወት ከመቀበላችን በፊት እኛን ማዳን አስፈላጊ ነበር። እግዚአብሔር ራሱ አዳምንና ሔዋንን በቆዳ አለበሳቸው፤ ስለዚህ ደም ፈሰሰ፣ ይህም እርቅ የሚመጣው ደም በማፍሰስ ብቻ መሆኑን ያሳያል። ታላቅ የኃጢአት ማስተስሪያ ቀን ነበር። ክርስቶስ እየሞተ ሳለ፣ ወደ እርሱ ለጠራው መለሰለት፡- "እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ።" (ሉቃስ 23: 43)። ከዚያች ከቀራኒዮ ቀን ጀምሮ፣ ሁሉም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በተሠራው የኃጢአት ማስተስሪያ በማመን እንደገና ወደ ገነት መግባት ይችላል።

በዚህ ዓለም የተወለደ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተለይቷል። ሁላችንም አዳምና ሔዋን እንዳደረጉት እንሠራ ነበር፤ ስለዚህ፣ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኞች ነን እና ሁላችንም መዳን ያስፈልገናል። የሚፈጸሙ የሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ከመዳናችን ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። እነርሱ በአዳምና በሔዋን በራሳቸው ላይ ከለበሱት የበለስ ቅጠል ጋር ሊነጻጸሩ ይችላሉ። ጌታ የሰው ዘርን የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ቃሉን ከተላለፉ በኋላ እንዳገኛቸው ሁሉ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ሁሉንም ያገኛል፣ ሁላችንም ትእዛዛቱን ተላልፈናልና ጥፋተኞች ነንና።

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሺህ ዓመታት ውስጥ፣ ጌታ ራሱን የገለጠላቸው ጥቂቶች ብቻ ነበሩ፣ እንደ ሄኖክ፣ ኖኅ፣ አብርሃም። የሰው ልጅ በራሱ መንገድ ተሳስቶ ጣዖት አምልኮን ይፈጽም ነበር። በሙሴ ዘመን፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ሕዝቡ እንዲሆን መረጠ። ትእዛዛት ተሰጡ እና ጌታ በዚይን ጊዜ እንደጠየቀዉ ሁሉም ነገር በሥርዓት ተቀመጠ ። መሥዋዕቶቹ የመጨረሻውን ቤዛነት መስጠት አልቻሉም ነበር፤ ኃጢአቶቹ የተሸፈኑ ብቻ ነበሩ። የዓለምን ኃጢአት ሊያስወግድ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ታላቅ በግ መሥዋዕት ይናገሩ ነበር። ከእግዚአብሔር የለየንን ነገር ያስወግዳል። ሕጉ አስፈላጊ ነበር፣ ምክንያቱም በእርሱ ብቻ ነው በኃጢአት ልንኮነን የምንችለው (ሮሜ 3: 20) እና ከዚያም የመዳንን አስፈላጊነት መገንዘብ የምንችለው። የእግዚአብሔር መንፈስ በተሰጡት ትእዛዛት መሠረት ያሳምነናል።እነርሱን መጠበቅ እንዳልቻልን እና ጥፋተኞች መሆናችንን በንስሓ እንናዘዛለን። ከዚያም አንድ ሰዉ የመዳንን አስፈላጊነትን ያያል።

በሰው አለመታዘዝ የመጣው ጊዜያዊ መቋረጥ የእግዚአብሔርን ከሰዉ ልጆች ጋር ያለዉን ዘላለማዊ ዕቅድ ሊያጠፋው አይችልም። በመተላለፍ ከእግዚአብሔር ተለይተን ነበር፣ ነገር ግን በእርቅ ወደ ህብረት እንደገና ተመልሰናል። እግዚአብሔር ተስፋ አልቆረጠም። እኛን የሚመልስበትን መንገድ አዘጋጀ። አዳነን፤ ሞትንና ሲኦልን ድል አደረገ፣ የዘላለም ሕይወትንም ሰጠን። እግዚአብሔርን

የምንቀርብበት መንገድ አልነበረንም። እኛ ወደ እርሱ መሄድ እንድንችል ፤ እርሱ ወደ እኛ መምጣት እና መንገድ ማዘጋጀት ነበረበት ። ሁሉም ሰው የኢሳይያስን 40: 3 ትንቢት ማወቅ አለበት፡- “በምድረ በዳ የሚጮኽ ድምፅ፡- ለጌታ መንገድ አዘጋጁ፣ በምድረ በዳ ለአምላካችን መንገድን ቀና አድርጉ።” በቁጥር 9 + 10 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “አንቺ መልካም ዜና የምታመጪ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ድምፅሽን በኃይል አንሺ፤ አንሺው፣ አትፍሪ፤ ለይሁዳ ከተሞች፡- እነሆ አምላካችሁ! እነሆ፣ ጌታ እግዚአብሔር በብርቱ እጅ ይመጣል፣ ክንዱም ለእርሱ ይገዛል።” በምዕራፍ 35: 4 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ልባቸው ለፈሩት፡- በርቱ፣ አትፍሩ፤ እነሆ፣ አምላካችሁ… ይመጣል ያድናችሁማል በሉ።” በምዕራፍ 52: 10 ላይ እንዲህ ይላል፡- “ጌታ ቅዱስ ክንዱን በሁሉም አሕዛብ ዓይኖች ፊት ገለጠ፣ የምድርም ዳርቻ ሁሉ የአምላካችንን ማዳን ያያሉ።”

አዳኙ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር መሆን ነበረበት። በሁሉም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት በጣም ግልጽ ነው። ለ4,000 ዓመታት ያህል አባት ከወልድ ጋር በሰማይ ሲነጋገር አንድም ጊዜ አናገኝም። እንደ መንፈሳዊ አካል፣ ሞትን ሊቀምስ አይችልም ነበር። ስለዚህ፣ በሥጋ አካል መገለጥ ነበረበት። እኛን ለማዳን እና ከውድቀት በፊት ወደነበርንበት የመጀመሪያ ሁኔታ ለመመለስ ይህ ብቸኛው መንገድ ነበር።

## የእግዚአብሔር ፍጥረት

እግዚአብሔር በመውለድ የአዲስ ፍጥረት መጀመሪያን አደረገ። የሰው ዘር በፍጥረት ተጀመረ። የእግዚአብሔር ዘር በመወለድ ይጀመራል። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የአባት-ልጅ ግንኙነት መመሥረት ነበረበት። ይህንን በአብርሃም፣ በሙሴ ወይም በሌላ በማንኛውም ነቢይ ሊያደርገው አልቻለም፣ ምክንያቱም ሁሉም በተፈጥሮ መፀነስ ወደዚህ ዓለም የተወለዱ ነበሩ። ስለዚህ፣ የወደቀው ፍጥረት አካል ነበሩ። ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መፀነስ፣ እግዚአብሔር የአዲስ ፍጥረት መጀመሪያን አደረገ። ይህ የሆነው በብቸኛ በወለደው ልጁ አማካኝነት ነበር። እግዚአብሔር የሕይወትን ዘር በድንግል ማርያም ውስጥ ፈጠረ። እርሷም የሕፃኑ ተሸካሚ ብቻ ነበረች። ማርያም እንዲህ አለች፡- “እነሆ የጌታ ባሪያ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ።” (ሉቃስ 1: 38)። አንድም ነቢይና አንድም ሐዋርያ እንዲሁም ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸው ስለ “እግዚአብሔር እናት” ምንም የሚያውቁት ነገር የለም። እግዚአብሔር እናት የኖረው ከመቼ ጀምሮ ነው? እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነውና ፈጽሞ አልተወለደም። ኢየሱስ ራሱ ማርያምን “እናት” ብሎ አንድም ጊዜ አልጠራም፣ ሁልጊዜ ግን “ሴት” ብሎ ይጠራት ነበር።

ክርስቶስ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ሆነ (ሮሜ 8: 29)። አዳም በፍጥረት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፣ ክርስቶስ ደግሞ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መፀነስ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። በእርሱ ብቻ ነው አዲስ ውልደት የምንቀበለውና በምድር ላይ የእግዚአብሔር ዘር አካል የምንሆነው። እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡- “እኛ ደግሞ ዘሩ ነንና። የእግዚአብሔርም ዘር ከሆንን፣ የእግዚአብሔርን አምላክነት እንደ

ወርቅ፣ ወይም እንደ ብር፣ ወይም እንደ ድንጋይ ማሰብ አይገባንም።" (ሐዋርያት ሥራ 17: 28 ሰ-29)።

እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት መጀመሩን ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት፣ ራእይ 3: 14 ን የበለጠ እንረዳለን፦ " አሜን የሆነዉ ፤ የታመነዉና እዉነተኛዉ ምስክር ፤ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረዉ እንዲህ ይላል።" ይህ የአጽናፈ ዓለምን ፍጥረት አይመለከትም፣ የሚያመለክተው በመለኮታዊ መፀነስ አዲስ ፍጥረት መፈጠርን ነው። ማርያም የተስፋውን ቃል እንደተቀበለችና በመንፈስ ቅዱስ እንደተጋረደች ሁሉ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች የተስፋውን ቃል መቀበል አለባቸው፣ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ አዲስ ሕይወትን ለማምጣት በእነርሱ ላይ ይመጣል። ጌታ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲህ አለ፦ "ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም።" (ዮሐንስ 3: 3)። በዚያው ምዕራፍ መንፈሳዊ ልደት እንዴት እንደሚከናወንም ተነግሮናል። በእርግጥ በሃይማኖታዊ ሥርዓት አይደለም። መለኮታዊው ዘር፣ እርሱም ቃል ነው፣ መጀመሪያ ወደ ነፍሳችን መግባት አለበት። ያለ መለኮታዊ ዘር አዲስ ልደትም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖር አይችልም። ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ከሐሰት ማስመሰል የዘለሉ አይደሉም። ሁሉም ከንቱ ናቸውና ለሰዎች ትልቁ እንቅፋት ናቸው። አዳኛችን እግዚአብሔር እና ሰው በተመሳሳይ ጊዜ መሆን ነበረበት፣ ነገር ግን ይኸን በስህተት ተረዱት።

በዮሐንስ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 33 ጀምሮ፣ አይሁድ ጌታችንን በስድብ ከሰሱትና እንዲህ አሉ፦ "...አንተ ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ታደርጋለህና። ኢየሱስም መለሰላቸው፦ እኔ አማልክት ናችሁ ብዬ ተናግሬአለሁ ተብሎ በሕጋችሁ አልተጻፈምን? የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ብሎ ከጠራ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም ሊሻር አይችልም፣ አብ የቀደሰውንና ወደ ዓለም የላከውን፣ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልኩኝ ትሳደባለህ ትላላችሁን?" በብሉይ ኪዳን የጌታ ቃል ወደ ነቢያት መጣ። በዚህ መለኮታዊ ነገር – በተቀበሉት ቃል – ምክኒያት አማልክት ተብለው ተጠሩ። ከእግዚአብሔር የሚወጣው መለኮታዊ የሆነ ነገር ብቻ ነዉ። ስለዚህ፣ ከእግዚአብሔር የሚወጣው ቃል መለኮታዊ ዘር መሆን አለበት (ሉቃስ 8: 11)፣ በእርሱም የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን። ያዕቆብ በምዕራፍ 1: 18 ላይ እንዲህ ሲል ጻፈ፦ "ከፍጥረቱ የበኵር ፍሬ እንድንሆን በፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን።"

ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህንኑ እውነታ በእነዚህ ቃላት አጽንዖት ሰጥቷል፦ " ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይድለም ፣ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነዉ እንጅ ።" (1ኛ ጴጥሮስ 1: 23)። ይህ ትምህርት ብቻ ሳይሆን፤ የግል ተሞክሮ መሆን አለበት። ውሳኔ ማድረግና ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል በእርግጥ በቂ አይደለም።

አሁን ወደ ዋናው ርዕሳችን ስለ አምላክነት እንመለስ። በብሉይ ኪዳን ወደ አራት ሺህ ዓመታት በሚጠጋው ጊዜ ውስጥ፣ ነቢያት እግዚአብሔርን "የሰማይ አባት" ብለው አልጠሩትም። ወደ ወልድ

የዞሩበት አንድም ዘገባ አናውቅም። በቀላሉ የለም። ይህን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ተስፋዎቹ በብሉይ ኪዳን ይገኛሉ፣ ፍጻሜያቸው ግን በአዲስ ኪዳን ነው። ከብሉይ ወደ አዲስ መሸጋገሩ ለመዳናችን ፍጹም አስፈላጊ ነበር። ከአዲስ ኪዳን ጋር አዲስ መገለጥ ተያይዞ ነበር፣ እና እኛ ልጆች ልንሆን ስለነበር፣ በወልድ መሆን ነበረበት። በተመሳሳይ ጊዜ፣ ያው የብሉይ ኪዳን ጌታ ያህዌ፣ በአዲስ ኪዳን ወልድ፣ ጌታ ኢየሱስ መሆኑን እንገነዘባለን።

የማይታየው አምላክ – ኤሎሂም በብሉይ ኪዳን ዘመን ራሱን በሚታይ እንደ ጌታ ገልጧል – ያህዌ ። ያው አምላክ አብ ነው፣ እርሱም በወልድ በግልጽ በሚታይ የሰው አካል ተገለጠ። "ኢየሱስ" – በዕብራይስጡ "ያህሹዓ" ማለት "ያህዌ-አዳኝ" ማለት ነው። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ስም በትክክል ያለበት ግንኙነት ውስጥ መተው አለበት። "አብ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ከዋለ፣ በፍጹም "ወልድ" በሚለው ቃል መተካት አይቻልም። "ወልድ" የሚለው ቃል ከተነገረ፣ በፍጹም "አብ" የሚለውን ቃል በምትኩ መጠቀም አይቻልም። ሁሉም ነገር ትክክለኛ ቦታና ቅደም ተከተል አለው፣ እንደ ፈጣሪ፣ አዳኝ፣ ንጉሥ፣ ዳኛ ወዘተ። የእግዚአብሔር የተለያዩ መገለጦች ሊለዋወጡ አይችሉም።

ብዙ ነገሮች የሆነው ያው አንድ አምላክ፣ በምድር ላይ በወልድ ራሱን ከገለጠ ወዲህ የሰማይ አባታችን ሆነ። እንደ አብ ፈጽሞ አልተወለደም፣ ፈጽሞም አልሞተም። እንደ ወልድ ግን ተወለደ፣ ተሠቃየ፣ ሞተ፣ ከዚያም እንደገና ተነሳ። እግዚአብሔር ስለ እኛ አላማ ነበረዉ፤ ስለዚህም በመዋጀት የእርሱ ዕቅድ አካል እንድንሆን ለእርሱ አስፈላጊ ሆነ። በሮሜ 6: 5 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር አንድ ከሆንን፣ ትንሣኤውን በሚመስል ትንሳኤ ከእርሱ ጋር አንድ እንሆናለን።" እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደተገለጠ ሁሉ፣ ክርስቶስም በአማኞቹ ይገለጣል፣ እርሱም ከሙታን እንደተነሳ ሁሉ፣ ለእርሱ የሆኑትም የመጀመሪያው ትንሣኤ አካል ይሆናሉ። "እግዚአብሔርም ጌታን አስነስቷል፣ እኛንም በራሱ ኃይል ያስነሳናል።" (1ኛ ቆሮንቶስ 6: 14)።

በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ውስጥ "ዘላለማዊ ወልድ" ወይም "ሰማያዊ ወልድ" የሚለው አገላለጽ አንድም ጊዜ እንደሌለ ማስተዋል እንዳለብን ይመከራል። ነገር ግን "ዘላለማዊ አምላክ" እና "ሰማያዊ አባት" የሚለውን እናገኛለን። ይህን ሁሉ በጥንቃቄ መመርመር አለብን። ለምሳሌ፣ ማንም፡- "እግዚአብሔርን አየሁ፣ ስለዚህም ጌታን አየሁ" አላለም፣ ነገር ግን ጌታን ያዩ ሁሉ፡- "እግዚአብሔርን አይቻለሁ" ሊሉ ይችላሉ። አብ፡- "ማንም እኔን የሚያየኝ፣ ወልድን ያያል" ሊል አልቻለም ፣ ወልድ ግን፡- " እኔን የሚያየኝ ሁሉ፣ አብን አይቷል" (ዮሐንስ 14: 9) ሊል ችሏል። እግዚአብሔርን የምናውቀው በመለኮታዊ መገለጥ ብቻ ነው። በተለያዩ መገለጦቹ አናቆምም፣ ወደ መነሻቸው ወደሆነው አንድ አካል እንመልሳቸዋለን። በሉቃስ 10: 22 ላይ እንዲህ ተነግሮናል፡- "…ወልድ ማን እንደሆነ ከአብ በቀር ማንም አያውቅም፤ አብም ማን እንደሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚዉቅ የለም አለ።"

እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አቅዷል። ክብሩም ቀድሞዉኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊገለጥ በዘላለም ዉስጥ ነበረ ። በቀደመዉ እዉቀቱ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ወንድ

ልጆቹና ሴት ልጆቹ የሚሆኑትን መምረጥ ችሎ ነበር (ኤፌሶን 1: 4-5)። ስማቸውን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት መጻፍ ችሎ ነበር (ራእይ 13: 8)። እውነተኛ የሆነ ቅድመ-ውሳኔ አለ። ክርስቶስ አዳኝ እንዲሆን አስቀድሞ ተወስኗል፣ ሙሽራውም እንድትድን አስቀድሞ ተወስኗል። እግዚአብሔር በቀደመዉ እዉቀቱ ቃሉንና ድነትን የሚቀበሉትን ማወቅ ችሏል። ስለዚህም፣ እንደዚሁ የዘላለም ሕይወትን ለእነርሱ አስቀድሞ ሊወስንላቸው ይችላል። በቀደመዉ እዉቀቱ ፣ ወደ ታላቁ ዕቅዱ አካትቶናል (ሮሜ 8: 29-30)።

## ትክክለኛ ለመሆን

ዛሬ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ፣ ቀሳውስት በረከትን ሲናገሩ፡- "የእግዚአብሔር አብ፣ የእግዚአብሔር ወልድ፣ እና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በረከት ከእናንተ ጋር ይሁን" የሚሉትን ልትሰሙ ትችላላችሁ። ነገር ግን እንዲህ ያለው አገላለጽ በአንድም ነቢይ ወይም ሐዋርያ አንድም ጊዜ ጥቅም ላይ እንዳልዋለ መገንዘብ አለብን። በእርግጥ እግዚአብሔር አባታችን ነው፣ ግን ደግሞ "እግዚአብሔር ወልድ" የሚለውን አባባል አታገኙም፣ ይልቁንም የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውን ታገኛላችሁ። ያው ለመንፈስ ቅዱስም ይሠራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንም ሰው "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" ብሎ ሲናገር አንድም ጊዜ አናገኝም። በውኃው ላይ ሰፍፎ የነበረዉ "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" አልነበረም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ነበር(ዘፍጥረት 1: 2)።

ሁሉም ነገር እንዴት እንደተለወጠ እና ወደላይና ወደ ታች እንደተደረገ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። በመሲሑ ላይ የወረደው "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" አልነበረም፣ ነገር ግን በቀላሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ነበር (ማቴዎስ 3: 16)። ማርያምን የጋረደው "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" አልነበረም፣ ነገር ግን እንደተጻፈው፡- "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህም ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።" (ሉቃስ 1: 35)። "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው አብ ሲጠራ ብቻ እንደሆነ ይገኛል፣ ለምሳሌ፡- "አምላክ እና አባት ይባረክ ..."፣ ነገር ግን ከወልድ ወይም ከመንፈስ ጋር ፈጽሞ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ የተለየ አካል ቢሆን ኖሮ፣ ሕፃኑ "የመንፈስ ቅዱስ ልጅ" ተብሎ መጠራት ነበረበት፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ማርያምን ጋርዶ ነበርና። መንፈስ ቅዱስ በቀላሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅም የአብ የራሱ የሚታይ መገለጥ ነው።

በኢዮኤል 2: 28 ላይ፣ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡- "መንፈሴን በሥጋ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ።" ፍጻሜውም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ ተመዝግቧል። እግዚአብሔር ሌላ አካልን አላፈሰሰም፣ እርሱ እንደተናገረው በቀላሉ መንፈሱን አፈሰሰ። በሐዋርያት ሥራ 1: 4-8 ላይ፣ ኢየሱስ ስለ አብ ተስፋ ተናገረ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን የመቀበል ተስፋ ነበር። እርሱ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ብቻ አልተናገረም (ዮሐንስ 16: 7)፣ ነገር ግን ራሱ እንደሚመለስ ቃል ገባ (ዮሐንስ 14: 18)። ሁለቱም እውነት ናቸው። በብዓለ ሃምሳ ዕለት፣ በመንፈስ አማካኝነት በአማኞች ውስጥ ኖረ። አሁን ክርስቶስ በመንፈስ መልክ በእኛ ውስጥ አለ ፣ የክብር ተስፋ ነው (ቆላስይስ 1: 27)።

ጴጥሮስ በመጀመሪያው ስብከቱ ላይ ያንን ታላቅ ክስተት ጠቅሷል (ሐዋርያት ሥራ 2: 33)፡- “እንግዲህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎ፣ ከአብም የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ተቀብሎ፣ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን ይህንን አፈሰሰ።” ሁሉም በጣም ቀላል ነው፣ የነገረ መለኮት ምሁራን ነገሮችን በጣም አወሳሰቧቸዉ። መጥምቁ ዮሐንስ ይህን ልምምድ በሚከተሉት ቃላት ቀድሞ አስታወቀ፡- “እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል።” (ማቴዎስ 3: 11)። እውነተኛው የሐዋርያዊ ትምህርት፣ በክርስቶስ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደነበረ፣ በመንፈስ ቅዱስም በእኛ ውስጥ እንደሚኖር ነው። በዮሐንስ 4: 24 ላይ፣ ጌታ እንዲህ አለ፡- “እግዚአብሔር መንፈስ ነው።” ስለዚህም ከመንፈሱ አፈሰሰ። በ2ኛ ቆሮንቶስ 3: 17 ላይ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- “ጌታም ያ መንፈስ ነው።” አሁን ምን ትላለህ? እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ ጌታ መንፈስ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ነው። ነገር ግን አንድ መንፈስ ብቻ አለ – ያም የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ “የእግዚአብሔር መንፈስ”፣ “የጌታ መንፈስ” ወይም “መንፈስ ቅዱስ” ቢልም፣ ያው አንድ አካል ማለት ነው። ስለ አብ፣ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ብናነብ፣ ነገሮችን ወደ መነሻቸው ብንመልስ፣ ሁልጊዜ ወደ ያው ምንጭ፣ እርሱም ሁሉን ቻይ ወደ ሆነዉ እግዚአብሔር ነው የምንደርሰው። ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ሊለያዩ አይችሉም። በወልድ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለውን ህብረት እንደገና መሠረተ፤ በመንፈስም ከእርሱ ጋር ህብረት አለን። ወልድ፡- “ከአብ ወጣሁ” አለ (ዮሐንስ 16: 28)። ያው ለመንፈስ ቅዱስም ተነግሯል፡- “…የእውነት መንፈስ፣ ከአብ የሚወጣ…” (ዮሐንስ 16: 26)። ስለዚህም ወልድና መንፈስ ከአብ በግራና በቀኝ ተቀምጠው አልነበሩም፣ ነገር ግን ከአብ ወጡ። ያ ፍጹም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው!

## ልጅነት

በመዝሙር 2: 7 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ትእዛዙን እናገራለሁ፡- ጌታ እንዲህ አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ፤ ዛሬ ወለድኩህ።” “ዛሬ” ወይም አንዳንድ ትርጉሞች እንደሚያስቀምጡት “በዚህ ቀን” ከዘላለም ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ስለ ጊዜ ይናገራል። በብሉይ ኪዳን ወደፊት የሚሆነው ነገር ተስፋ ነበር። አሁን ወደ ኋላ ስንመለከት ተፈጽሞ እናየዋለን። የመዳን ዕቅድ ሁሉ በብሉይ ኪዳን በትንቢታዊው ቃል ተቀምጦ ነበር፤ ነገር ግን የእያንዳንዱ ተስፋ ፍጻሜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይከናወናል። በመዝሙር 2: 8 ላይ ስለ ወልድ እንዲህ እናነባለን፡- “ለምነኝ፣ አሕዛብንም ለርስትህ ፣ የምድርንም ዳርቻ ሁሉ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ።” በቁጥር 7 እና 8 ላይ ስለ ወልድ እና ስለ ሁሉም አሕዛብ እንደ ርስት ለእርሱ እንደሚሰጡት እንሰማለን። የእግዚአብሔርን መኖር በማመን ብቻ ማንም ሊድን እንደማይችል ለሁሉም ግልጽ መሆን አለበት፣ ምክንያቱም ሰይጣንም ያምናልና ይንቀጠቀጣል (ያዕቆብ 2: 19)። የሚቤዥዉ፣ የሚያድነዉ እምነት አንድ እውነተኛ አምላክ በወልድ አማካኝነት ከራሱ ጋር እንዳስታረቀን ማመን ነው። አንድ ሰው እግዚአብሔር በቀጥታ በክርስቶስ መገለጡን ካላመነ፣ በቀላሉ ጠፍቷል። መጽሐፍ ቅዱስ አሁንም ትክክለኛ ነው፡- “በጌታ በኢየሱስ

ክርስቶስ እመን፣ አንተም ቤትህም ትድናላችሁ።" (ሐዋርያት ሥራ 16: 31)። ወልድ አዳኛችን ሆነ፤ ስለዚህ፣ ለመዳን በእርሱ ማመን አለብን።

በመዝሙር 2: 12 ላይ፣ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ብርሃን እያረፈበት ነው። "ወልድን ሳሙት፣ ምናልባት እንዳይቆጣ፣ ቁጣው ጥቂት ቢነድድ ከመንገድም እንዳትጠፉ። በእርሱ ላይ የሚተማመኑ ሁሉ ብፁዓን ናቸው።" የሚለውን አባባል እናገኛለን። ይህን ቃል ቀላል አድርገን ልናልፈው አንችልም። ብዙዎች ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ አፍቃሪው ሰማያዊ አባት ይናገራሉ፣ ነገር ግን አብ በወልድ አማካኝነት አዳኛችን እንደሆነ አይገነዘቡም። ስለዚህ፣ በእውነት በአብ ማመን የሚጀምረው በወልድ በማመን ነው፣ ምክንያቱም መዳናችን በወልድ ተከናውኗልና። በእግዚአብሔር ብቸኛዉ ዋጋ ያለዉ እምነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለው እምነት ነው። በእርሱ ብቻ ነው እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር በአካል የተገናኘው፣ በእርሱም እግዚአብሔርን ልናገኝና ልንድን እንችላለን። እርሱ ለእኛ ሲል በተገለጠው መንገድ በእርሱ ማመን አለብን።

በእኛ ምክንያት፣ አባት-ልጅ ግንኙነት መመሥረት ነበረበት። እኛ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ልንሆን ነበር። በ2ኛ ሳሙኤል 7: 14 ላይ፣ ትንቢታዊውን ማስታወቂያ እናገኛለን፦ "እኔም አባት እሆናለሁ፣ እርሱም ልጄ ይሆነኛል።" ግን በዚህ አያቆምም። እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆቹን ሁሉ በትልቁ ፕሮግራሙ ውስጥ ያካትታል። በሆሴዕ 1: 10 ለ ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "ሕዝቤ አይደላችሁም በሚባልበት ፤በዚያ ስፍራ ስለነእርሱ የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ይባላል።" ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ተቻለ። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 6: 18 ላይ እንዲህ ይላል፦ "...እኔም አባት እሆናችኋለሁ፣ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ ትሆናላችሁ ይላል ሁሉን ቻይ ጌታ።" ሁሉም እውነተኛ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ታዛዦች ይሆናሉ እና ታማኝነታቸውን ያረጋግጣሉ።

በኤፌሶን 1: 5 ላይ፣ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ከእኛ ጋር አጽንዖት በመስጠት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡"..በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ለእርሱ ልጆች እንሆን ዘንድ አስቀድሞ ወሰነን።" ስለ እግዚአብሔር እና ከሰው ልጆች ጋር ስላለው ዕቅድ እየተነጋገርን ነው። በምድር ላይ የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል መሆን ምን ማለት እንደሆነ የሚገነዘቡ ሰዎች አሉ። በክርስቶስ ተመርጠዋል፣ በእርሱ ውስጥ ናቸው። ስለዚህ፣ በእነርሱ ላይ ምንም ክስ አይቀርብም። በቤዛነት አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ጽድቅን ተቀብለዋል። እንደ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ተቀምጠዋልና እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛሉ።

ከአብና ከወልድ ግንኙነት ጋር በተያያዘ፣ በመዝሙር 89፣ ቁጥር 26-27 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ " እርሱ አባቴ አንተ ነህ ፣ አምላኬ፣ የመዳኔቱ ዓለት ነህ ብሎ ይጮህልኛል። እኔም ደግሞ በኵሬ አደርገዋለሁ፣ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ።" ይህ በብሉይ ኪዳን ትንቢት ነበር፣ ፍጻሜውንም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እናያለን። በሥጋው አካል ውስጥ፣ ብቸኛው ልጅ ሆኖ ተሠቃየና ሞተ፣ የሁሉንም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ቦታ ወሰደ።

በትንሣኤው አማካኝነት፣ አካሉ ከሟችነት ወደ ዘላለማዊነት ተለወጠ:: በዚህ እውነታ፣ ትንሣኤያችንና የአካላችን መለወጥ የተረጋገጠ ነው::

ሰዎች ስለሱ ለመወያየት የሚፈልጉት ትምህርትን ብቻ አይደለም የምንመለከተው:: የሰው ልጆችን የሚወስድና የእግዚአብሔር ልጆች የሚያደርግ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ መፈጸምን ነው:: ኃጢአታችንን ከእኛ መወሰድ ብቻ ሳይሆን፣ ከሞትም መዳንና ከሲኦል ነጻ መዉጣት ነበረብን:: በመዝሙር 68: 19-20 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ ዕለት ዕለት ጥቅምን የሚያከናውንልን ጌታ የተባረከ ይሁን ፣ የመዳኛችን አምላክ:: አምላካችንስ የደህንነተ አምላክ ነው፤ ከሞት መውጣትም በጌታ በእግዚአብሔር ነው::”

ወደዚህ ዓለም ከተወለደ ማንም ሰው በሞት ላይ ሥልጣን ያለዉ አልነበረም:: በተቃራኒው፤ ሄኖክና ኤልያስን ሳይጨምር ሁሉም በሞት ተወሰዱ:: በዙሪያችን ብዙ መቃብሮች አሉ:: መምጣትና መሄድ ነው:: ግን ጌታ እንዲህ አለ፡- “ከሲኦል እጅ እታደጋቸዋለሁ እቤዣቸዉ፤ ከሞትም እቤዣቸዋለሁ አድናቸዋለሁ:: ሞት ሆይ፣ ቸነፈርህ ወዴት አለ?ሲኦል ሆይ፤ ማጥፋትህ ወዴት አለ? ርህራሔ ከአይኔ ተሰወረች::” (ሆሴዕ 13: 14)::

ይህ በብሉይ ኪዳን የተገባ ተስፋ ነበር – አሁን ግን እውነት ነው:: ሞትን፣ ሰይጣንንና ሲኦልን ስለ እኛ ድል የነሳውን እናውቃለን:: በዘካርያስ 9: 11 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ለአንችም ደግሞ ስለቃል ኪዳንሽ ደም እስሮችሽን ውኃ ከሌለበት ጉድጓድ አዉጥቻለሁ::” ስለ አልዓዛር እና ዉሃ ስለለመነዉ ሀብታሙ ሰው እናውቃለን::

የኃጢአት ማስተስሪያው መሲሑን ይመጣል ብለዉ ለጠበቁትም ነበር:: እነርሱ ወደ ገነት ገቡ፣ ነገር ግን ክርስቶስ ሲነሳ፣ የመጀመርያው ትንሣኤ አካል መሆን የነበረባቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ከእርሱ ጋር ከመቃብር ወጡ (ማቴዎስ 27፣ ከቁጥር 51 ጀምሮ):: በኤፌሶን 4: 8 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ስለዚህም እንዲህ ይላል፡- ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ፣ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ”

አዲስ ቃል ኪዳን ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተስፋ ተደርጎ ነበር:: እኛ የምንመለከተው በመለኮት የተረጋገጠ እውነታ ነው:: ነቢዩ ኤርምያስ በምዕራፍ 31: 31-34 ላይ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- “እነሆ፣ አዲስ ቃል ኪዳን የማደርግበት ቀን ይመጣል፣ ይላል ጌታ... ከአባቶቻቸው ጋር እንደ አደረግሁት ቃል ኪዳን አይደለም... ነገር ግን ለእስራኤል ቤት የማደርገው ቃል ኪዳን ይህ ይሆናል፡ - ከእነዚያ ቀናት በኋላ፣ ይላል ጌታ፣ ሕጌን በውስጣቸው አኖራለሁ፣ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ አምላካቸውም እሆናለሁ፣ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ:: ከእንግዲህም ማንም ሰው ባልንጀራውንና ማንም ወንድሙን፡- ጌታን እወቅ! እያለ አያስተርም፤ ከታናናሾቻቸው እስከ ታላላቆቻቸው ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና፣ ይላል ጌታ፤ ዓመፃቸውን እምራለሁና፣ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብም::”

ጌታ እግዚአብሔር የሚከተለውን ተስፋ ሰጠ እናም የሚቻል አደረገው፡- "አዲስ ልብንም እሰጣችኋለሁ፣ አዲስ መንፈስንም በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋይ ልብንም ከሥጋችሁ አወጣለሁ፣ የሥጋ ልብንም እሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ፣ በትእዛዜም እንድትሄዱ አደርጋችኋለሁ፣ ሥርዓቴንም ትጠብቃላችሁ፣ ታደርጓቸዋላችሁም።" (ሕዝቅኤል 36: 26-27)።

አሁን ወደ ታላቁ የኃጢአት ማስተስሪያ ቀን እንመለከታለን፣ እርሱ ዓመፃችንን ይቅር እንዳለን እና ኃጢአታችንንም ከእንግዲህ እንደማያስብ አዉቀን። አዳኛችን ሲሞት፣ አዲሱ ቃል ኪዳን ተመሠረተ። እርሱ ራሱ ከመከሰቱ በፊት በማቴዎስ 26: 28 ላይ ስለሱ መስክሯል፡- "...ይህም የብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚሆን የአዲሱ ቃል ኪዳን ደሜ ነውና።" ወንጌላት አዳኛችን ሲሞት ምን እንደተከናወነ የተዘገቡትን ይዘዋል። ከትንሣኤው በኋላ ያዩት ምስክሮችም ነበሩ። ይህ ታሪክ ሳይሆን ፤ ይህ እውነት ነው። እርሱ እንደ ታላቅ አሸናፊ ወጣ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለዚሁ ታላቅ ክስተት እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "...ክርስቶስ ደግሞ ኃጢአት ሳይሠራ ስለ ኃጢአት አንድ ጊዜ መከራን ተቀበለና፣ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን በሥጋ ሞቶ፣ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ።" (1ኛ ጴጥሮስ 3: 18)። ውድ በሆነ ዋጋ ተገዝተናል። ቤዛነት አግኝተናል፣ ነፃ ወጥተናል። ሞትና ሲኦል በእኛ ላይ የነበራቸውን የይገባኛል ጥያቄ አጥተዋል። እግዚአብሔር በቃሉ የሚናገረውን በቀላሉ እናምናለን፡- "ልጆችም ሥጋና ደም የሆኑ እንደመሆናቸው መጠን፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ስልጣን ያለዉን በሞት እንዲሽር ይኸዉም ዲያብሎስ ነዉ ፣ በሕይወታቸው ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ ፤ በስጋ እና በደም ተካፈለ ።" (ዕብራውያን 2: 14-15)። በሦስተኛው ቀን ሲነሳ የቤዛነትን ሥራ ጨረሰ። ከዚያም ለአርባ ቀናት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆየ፣ ለእነርሱ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገር እየነገራቸዉ። በኋላም በደቀ መዛሙርቱ ፊት ወደ ሰማይ ተወሰደ (ሉቃስ 24: 50-51)። ተዛማጅ የመጻሕፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሁላችንም ይታወቃሉ።

የሚያስደንቀው ክፍል ደግሞ ሁሉም ነገር በብሉይ ኪዳን ተተንብዮ እና ቀድሞ ተነግሮ እና ከዚያም በአዲስ ኪዳን ተመስክረና ታየ። በመዝሙር 68: 18 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ወደ ላይ ወጣህ፣ ምርኮንም ማረክህ።" ተመሳሳይ ትንቢት በመዝሙር 47: 5 ላይ ይገኛል፡- "እግዚአብሔር በእልልታ ዓረገ ፣ ጌታ በመለከት ድምፅ።" ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ እንዳለ ሁላችንም እናውቃለን፣ ነገር ግን ሥጋ ለብሶ የተገለጠ እግዚአብሔር እንደነበረም እንገነዘባለን። ስለዚህም እግዚአብሔር በእልልታ ከፍ ከፍ ማለቱ እውነት ነው። የእግዚአብሔር ዕቅድ ከሰው ልጆች ጋር እውን ሆነ። በኤፌሶን 4: 10 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- " ይህ የወረደው ሁሉንም ይሞላ ዘንድ፣ ከሰማያትም ሁሉ በላይ የወጣዉ ደግሞ ያዉ ነው።"

በጉዳዩ ላይ ሌሎች በርካታ የመጻሕፍ ቅዱስ ጥቅሶችን መስጠት እንችላለን። ይህን ምዕራፍ በሚከተለው መግለጫ እንጨርሳለን፡- "' እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ

እንዲህ ብዬ ፡- መጻህፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም፣ መጻሐፍ እንደሚል በሦስተኛውም ቀን ተነሳ፤ ለኬፋም ታየ፣ ከዚያም ለአሥራ ሁለቱ። ከዚያማ በኋላ፣ ከአምስት መቶ በላይ ለሆኑ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፣ ከእነርሱም አብዛኞቹም እስከ አሁን አሉ አንዳንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል። ከዚያ በኋላ ለያዕቆብ ታየ በኋላም ለሁሉም ሐዋርያት ታየ። በመጨረሻም እንደጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየ ።" (1ኛ ቆሮንቶስ 15: 3-8)።

## የክርስቶስ ሰዉ መሆን

አሁን ደግሞ የክርስቶስን ሰዉ መሆንን እንመለከታለን። ከእግዚአብሔር በተጨማሪ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የሰው ልጅ፣ የዳዊት ልጅ፣ የእግዚአብሔር በግ፣ አማላጅ፣ ጠበቃ፣ ነቢይ ወዘተ ተብሎ ታይቷል። ስለ እርሱ እንዲህ እናነባለን፡- "...ራሱን ባዶ አደረገ፣ የባሪያንም መልክ ያዘ፣ በሰውም ምሳሌ ሆነ፤ በሰው አምሳልም ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም የታዘዘ ሆነ፣ እስከ መስቀል ሞት እንኳ።" (ፊልጵስዩስ 2: 7-8)። የክብር ጌታ ባሪያ ሆነ፤ ያህዌ እንደ ያህሹዓ ተገለጠና ልክ እንደ ማንኛውም ሌላ ልጅ ወደዚህ ዓለም ተወለደ (ሉቃስ 2: 7)። እኛን ለማዳን፣ ሎጎስ – ቃል – ሥጋ መሆን ነበረበት (ዮሐንስ 1: 14)። እርሱ መቶ በመቶ ሰው ነበር። እንደ ሕፃን በሕጉ መሠረት ተገረዘ፡- "ሕፃኑንም ለመገረዝ ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ፣ ስሙ ኢየሱስ ተባለ፣ እርሱም በማኅፀን ሳይጸነስ በፊት በመልአኩ የተሰጠ ስም ነበር።" (ሉቃስ 2: 21)።

እርግጥ ነው፣ ይህ መረዳት ከምንችለው በላይ ሊሆን ይችላል። ግን በእምነት የእርሱ የታላቁ ዕቅድ አካል የሆነውን ሁሉ እንቀበላለን። የክርስቶስ መወለድ በተነገረ ጊዜ፣ መልአኩ እንዲህ አለ፡- "...ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና።" (ማቴዎስ 1: 21)። ይህ ሕፃንም ለእግዚአብሔር ተሰጥቷል፣ በሉቃስ 2: 22-23 ላይ እንደምናነበው፡- "...ወደ ኢየሩሳሌምም አመጡት፣ ለጌታ ሊያቀርቡት፣ በጌታ ሕግ እንደተጻፈው፡- ማኅፀንን የሚከፍት ወንድ ሁሉ ለጌታ ቅዱስ ይባላል።" እርሱም በተፈጥሮ በኵር ነበር፣ ማርያም በኋላ ከዮሴፍ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆች ስለነበሯት (ማቴዎስ 13: 55-56)።

ይህን ታላቅ ምስጢር ለመረዳት መሞከር ትርጉም የለውም፤ እኛ ዝምብለን እናምናለን። በአንድ ስፍራ እንዲህ እናነባለን፡- "ዛሬ በዳዊት ከተማ አዳኝ እርሱም ክርስቶስ ጌታ ተወልዶላችኋልና።" (ሉቃስ 2: 11)፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕፃኑ እንደ በኩር ለጌታ እንደተሰጠ ተነግሮናል። በአዲስ ኪዳን የተከናወኑትን ነገሮች ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር ማየቱ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ያህዌ በመንፈሳዊው አካል የሚታይ የመገለጥ ዓይነት እንደነበረ ሁሉ፣ ኢየሱስም በሥጋ አካል የሚታይ መገለጥ ነበር።

ሰዉን ለመረዳትና ለማዳን መቶ በመቶ ሰው መሆን ነበረበት። ማስመሰል አልነበረም፣ እውነት ነበር። እርሱ ተሠቃየና አለቀሰ፣ በሁሉም መንገድ እኛ እንደሆንን ሆኖ ተገኘ፣ ግን ያለ ኃጢአት።

ለመሞት፣ ሰው መሆን ነበረበት። ሞትን፣ ሲኦልንና ሰይጣንን ለማሸነፍ፣ እግዚአብሔር መሆን ነበረበት። ሰዉ በመሆኑ ይበላና ይጠጣ ነበር፣ ይደክም ነበርና ይተኛም ነበር፣ እኛ እንደምንጸልየው ይጸልይ ነበር – በሁሉም መንገድ ሰው ነበር።

በዕብራውያን 2: 17 ላይ እንዲህ ተብሎልናል፦ "ስለዚህም የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፣ ለእግዚአብሔር በሆነዉ ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፣ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባዉ።"

የምንወደውን ጌታችንን በምናይበት ጊዜ ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር በተጨማሪ ሰዉ መሆኑን እናየዋለን። ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፣ ወደዚህ ዓለም የተወለደ። እኛም ለአምላክ ልንለይና ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች ልንሆን ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 1: 4)። ስለዚህ፣ ደሙ፣ ሀሳቦቹ፣ ሕይወቱ – ሁሉም ነገር ፍጹም ቅዱስና ንጹሕ ነበር። ሞት በእርሱ ላይ የይገባኛል ጥያቄ አልነበረውም፣ ሲኦልም ሆነ ሰይጣንም። ነገር ግን የእኛን ቦታ ወሰደ፣ በእኛ ላይ የመጣውን ሁሉ በራሱ ላይ ወሰደ። አራቱ ወንጌሎች መሲሑን ከመወለዱ አንስቶ ወደ ሰማይ እስከ ማዕረጉ ድረስ በሰዉ ልጅነቱ ይገልጹታል። እርሱ ፍጹም ታዛዥነትን አሳይቷልና እንደ ሌሎቹ ሕዝብ ሁሉ በዮሐንስ ተጠመቀ። ስለዚህ፣ በሉቃስ 3: 21-22 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "ሕዝቡ ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ፣ ኢየሱስም ተጠምቆ ሲጸልይ፣ ሰማይ ተከፈተ፣ መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፣ ከሰማይም፦ አንተ የምወደህ ልጄ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ መጣ።"

እኛ የምንጨነቀው ስለ አንድ ታላቅ ክስተት ብቻ አይደለም፣ ለእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሁሉ ያለውን አተገባበር መረዳት አለብን። በእውነት የሚያምን ሁሉ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ይሆናልና በመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ ይጠመቃል። ሰማይ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ እንደተከፈተና መንፈሱም በእርሱ ላይ እንደወረደ ሁሉ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሰማይ ሲከፈት ያያሉና መንፈስ ቅዱስም በብዓለ ሃምሳ ቀን እንደነበረው በእነርሱ ላይ ይመጣል። በውኃ ጥምቀት ክርስቶስን እንደተቀበልን እናሳያለን፤ በመንፈስ ጥምቀት እግዚአብሔር እኛን እንደተቀበለን ይናገራል። ይህ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል አስፈላጊ ነው፣ ስለዚህም እንደ ልጆቹ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሕይወት መምራት እንችላለን።

## አገልጋዩ

ሰዉ በመሆኑ፣ ክርስቶስ እንደ አገልጋይ ተነግሯል። እንደዚያም ሆኖ፣ የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ ለማድረግ መጣ። ኢሳይያስ 42: 1 እንዲህ ይላል፦ "እነሆ፣ ደግፌ የያዝኩት ባሪያዬ፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ መንፈሴን በእርሱ ላይ አድርጌአለሁ፤ እርሱም ለአሕዛብ ፍትሕን ያወጣል።" ይህ በብሉይ ኪዳን የተገባ ተስፋና ትንቢት ነበርና በአዲስ ኪዳን የተፈጸመ እውነታ ሆነ።

ሁሉም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች በኢየሱስ ክርስቶስ በወልድ አማካኝነት በሰማያዊ አባት ዘንድ ተቀባይነት አገኙ።

የእግዚአብሔር መንፈስ በክርስቶስ ላይ ከወረደ በኋላ፣ የተቀባው መሲሕ ሆነና አገልግሎቱን ጀመረ። በሉቃስ ምዕራፍ 4፣ ከቁጥር 18 ጀምሮ፣ የኢሳይያስን 61: 1-2 ስለ እርሱ የተነገረውን ትንቢት እንዲህ ሲል አነበበ፡- "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ የተሰበረ ልብ ያላቸውን እንድፈውስ፣ ለታሰሩት ነፃነትን፣ ለዕውሮችም ማየትን፣ የታመሙትን ነፃ እንዳወጣ፣ የተወደደውን የጌታን ዓመት እንድሰብክ ልኮኛል።"

በእግዚአብሔር የታቀደው ዕቅድና ዓላማ እየተፈጸመ ነው። ክርስቶስ ከሙታን ስለተነሳና ቤዛነት ባገኙት ውስጥ ስለሚኖር፣ አገልግሎቱን በእነርሱ አማካኝነት ይቀጥላል። የጠፉት ይድናሉ፣ የታሰሩት ነፃ ይወጣሉ፣ የታመሙትም ይፈወሳሉ፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው። እኛ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት የፈጸመዉ ቃል ኪዳን አካል ነን። በኢሳይያስ 42: 6-7 ላይ እንዲህ ይላል፡- "እኔ ጌታ፣ በጽድቅ ጠርቼሃለሁና፣ እጅህንም እይዛለሁ እጠብቅሃለሁም፣ የዕዉሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ የተዘጋዉንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብም ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ" ይህ ትንቢት እውነት እንደሆነ እናውቃለን። ፍጻሜውም በማቴዎስ 12: 17-21 ላይ ሊነበብ ይችላል፡- "...በነቢዩ በኢሳይያስ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ እንዲህ ሲል ፡- እነሆ የመረጥኩት ባሪያዬ፤ ነፍሴ እጅግ ደስ የተሰኘችበት የምወደው፤ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፣ ለአሕዛብም ፍትሕን ያሳያል። አይጣላም፣ አይጮኽም፤ ድምፁንም በአደባባይ ማንም አይሰማም። የተቀጠቀጠንም ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጨስን የጥዋፍ ክር አያጠፉም፣ ፍትሕንና ድልን እስኪያወጣ ድረስ። በስሙም አሕዛብ ይታመናሉ።"

ነቢዩ ኢሳይያስ ቤዛውን በስቃዩ ዉስጥ እን ደአገልጋይ በምዕራፍ 52 ከቁጥር 13 ጀምሮ፣ እስከ ምዕራፍ 53: 12 ይገልጻል። ነቢያት የእርሱን መንገድ ወደ ጌቴሴማኒና እስከ ቀራኒዮ ድረስ በመለኮታዊ መገለጥ አይተዉታል። ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "...እርሱን ባየነው ጊዜ፣ የምንፈልገው ውበት አልነበረውም። የተናቀ፣ በሰዎች የተጠላ፣ የሐዘን ሰው፣ ከሥቃይ ጋር የተዋወቀ ነበር፣ ፊታችንንም ከእርሱ እንደ መደበቅ ነበርን፤ የተናቀ ነበር፣ እኛም ምንም አላሰብነውም። እርግጥ ነው ሐዘናችንን ተሸከመ፣ ሥቃያችንንም ተሸከመ፤ እኛ ግን የተመታ፣ በእግዚአብሔር የተመታና የተጎዳ መስሎን ነበር። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፣ ስለ በደላችንም ተጎሳቈለ፤ የሰላማችን ቅጣት በእርሱ ላይ ነበር፣ በመገረፉም ቁስል ተፈወስን።" (ምዕራፍ 53: 2 ሰ-5)።

በመዝሙር 129: 3 ላይ፣ ሥቃዩ አስቀድሞ እንዲህ ተነግሯል፡- "አራሾች በጀርባዬ አረሱ፤ ቦያቸዉን ረጅም አደረጉ።" እርሱ ይህን ሁሉ ሥቃይ ማለፍ የነበረበት ለምን እንደሆነ ልንገረም እንችላለን፣ ነገር ግን ቅጣታችንን መውሰድ ነበረበት። ጥፋተኞች እኛ ነበርን። በኢሳይያስ 50: 6 ላይ፣ ተመሳሳይ

ሀሳብ እንዲህ ሲል ተገልጿል፦ “ጀርባዬን ለሚመቱ ሰጠሁ፣ ጉንጨንም ፀጉሬን ለሚነጭ፤ ፊቴን ከነፍረትና ከተፋት አልሸሸግሁም።” እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ ጌታችንና አዳኛችን እንዴት እንደተሳለቀበት፣ እንደተደበደበ፣ እንደተተፋበት ወዘተ ያውቃል። ነቢያት የተነበዩት ሁሉ ተፈጽሟል።

እንደ አገልጋይ፣ መሲሑ ምናልባት ማንም ሰው በማነኛዉም ጊዜ ከሚዋረደዉ በላይ ተዋርዷል። በምድር ላይ ከባድ ወንጀለኛ እንደሆነ ተድርጎ ተቆጠረ። በማርቆስ 14: 65 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ “አንዳንዶችም በእርሱ ላይ መትፋት ጀመሩ፣ ፊቱንም ይሸፍኑት ነበር፣ ይመቱትም ነበር፣ ትንቢትም ተናገር ይሉት ነበር። ጠባቂዎቹም በእጃቸው መዳፍ መቱት።” የክብር ጌታ የሐዘን፣ የዕንባና የሥቃይ ሰው እንደሆነ ማን ሊረዳ ይችላል? በማርቆስ 15 ላይ፣ በራሱ ላይ ስለተደረገው የሾህ አክሊል፣ አሾፊዎች እንዴት እንደተሳለቁበት ማንበብ እንችላለን። በቁጥር 28 ላይ፣ ማብራሪያው ተሰጥቷል፦ “መጻሕፍትም ከኃጢአተኞች ጋርም ተቈጠረ የሚለዉ ተፈጸመ።”

በስቃዩ ውስጥ እንደ ንጉሥ በውበቱ አናየውም፤ ሁሉንም የሰውን ሸክም የተሸከመ አገልጋይ ሆኖ እናየዋለን። ነቢዩ ኢሳይያስ የሥቃዩ ፍሬ ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ተንብዮ ነበር፦ “የነፍሱንም ድካም ያያልና ይረካል። ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙዎችን ያጸድቃልና፤ በደላቸውንም ይሸከማል። ” (ምዕራፍ 53: 11)። እርሱ ጌታ ነበር፣ ግን እንደ አገልጋይ መሥራት ነበረበት። ሞት የሚገባን ጥፋተኞች እኛ ነበርን፣ ነገር ግን በእምነት ጸድቀናል። በእግዚአብሔር ተጥለን ነበር፣ ነገር ግን መስቀል ላይ ሲሞት ቦታችንን ወሰደ፣ በታላቅ ድምፅም ጮኸ፦ “አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውከኝ?” ያ የዓለም ኃጢአት ሁሉ በእርሱ ላይ የተደረገበት ቅጽበት ነበር። እግዚአብሔር ኃጢአትን ሊታገስ አይችልም፣ ስለዚህ በዚያን ጊዜ ራሱን አገለለ፣ ነገር ግን በሚቀጥለው ቅጽበት ጦሩ ወደ ጎኑ ተወጋ፣ ቅዱስ ደም ለመዳናችን ፈሰሰ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ታረቅን።

በመዝሙር 22: 1 ላይ፣ ዳዊት በመለኮታዊ መነሳሳት ይህ እንደሚሆን ትንቢት ተናግሮ ነበር። በቁጥር 7 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ “የሚያዩኝ ሁሉ ያሾፉብኛል፤ ከንፈራቸውን ያጣምማሉ፣ ራሳቸውንም ይነቀንቃሉ።” እንደተናገረው እንዳደረጉት ከታሪኩ እናውቃለን። ዳዊት በቁጥር 16-18 ላይ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፦ “ውሾች ከበቡኝና፤ የክፉዎችም ጉባኤ ያዘኝ ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፣ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።”

በብሉይ ኪዳን የተሰጡ ከመቶ በላይ ትንቢቶች በክርስቶስ የመጀመሪያ ምፅዓት እንዴት በትክክል እንደተፈጸሙ በእርግጥ ተረድተናልን? ከመወለዱ አንስቶ ወደ ሰማይ እስከ ማረጉ ድረስ ሁሉም ነገር ተተንብዮ ነበርና እውነት ሆነ። ሐዋርያው ጴጥሮስ የሚከተለውን መግለጫ ይሰጣል፦ “...የእምነታችሁን ፍጻሜ፣ የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ። ነቢያት ይህን ድነት በጥንቃቄ መርምረዋልና ፈለጉት፣ ለእናንተ ሊመጣ ስላለው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት፣ በውስጣቸው የነበረው የክርስቶስ መንፈስ የክርስቶስን መከራና የሚከተለውን ክብር አስቀድሞ የመሰከረው ምንን ወይም

የትኛውን ዘመን እንደሚያመለክት ይፈልጉ ነበር።" (1ኛ ጴጥሮስ 1: 9-11)። የእግዚአብሔር መንፈስ ለነቢያት ምን እንደሚሆን እንደገለጠላቸው ሁሉ፣ አሁን ወደ ኋላ ተመልክተን ያው መንፈስ ቅዱስ ባሳየው መገለጥ ስለ እኛ እንደተፈጸመ እናያለን። ጳውሎስ በኤፌሶን 2: 13-16 ላይ እንዲህ ሲል በሚያምር ሁኔታ ይገልጸዋል፦ "አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና፣ ሁለቱን አንድ ያደረገ በአዋጅ የተነገሩትን የትእዛዛት ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ  በስጋዉ ያፈረሰ ፤ ይህም ከሁለታቸዉ አንድን አዲስ ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ፤ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸዉን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነዉ።"

 እኛ ተጠቃሚዎች ነን፣ በእምነት እግዚአብሔር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ያደረገንን ያንን እንደሆንን እንገነዘባለን። በአለመታዘዝና በኃጢአት ሰይጣን ያደረገን አይደለንም። የዘላለም ሕይወትን አግኝተን፣ እንደገና የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወደመሆን ቦታ መመለሳችንን በፍጹም ቤዛነት እንደሆነ እንገነዘባለን።

ጌታችን ይህንን መንገድ በእኛ ምክንያት መሄድ እንደነበረበት ስናስብ፣ እጅግ ትንሽነት ይሰማናል። አስደናቂ ጸጋው በእኛ ላይ ተሰጥቶናል፣ ፍቅሩም ወደ እኛ ተገለጠ። እርሱ ጌታና መምህር ሆኖ (ዮሐንስ 13: 13)፣ እንደ አገልጋይ ሲሠራ እንዲሁ እንዲጠራ አልፈለገም። "አንድ ገዥም ጠየቀውና፦ መልካም መምህር፣ የዘላለም ሕይወትን ለመውረስ ምን ላድርግ? ኢየሱስም አለው፦ መልካም ለምን ትለኛለህ? ከእግዚአብሔር በቀር ማንም መልካም የለም።" (ሉቃስ 18: 18-19)።

ሰዉ እንደመሆኑ ስናየው፣ ከማንም ክብርን ወይም መከበረን አልወሰደም። በዮሐንስ 5: 41 ላይ እንዲህ አለ፦ "ክብርን ከማንም አልቀበልም።" በቁጥር 44 ላይ፣ እንዲህ አለ፦ "እርስ በርሳችሁ ክብርን እየተቀበላችሁ፣ ከእግዚአብሔር ብቻ የሚመጣውን ክብር የማትፈልጉ እንዴት ታምናላችሁ?" ይህም እንደ አገልጋይ ያለውን ሚና ያሳያል። እንደዚያም ሆኖ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግና የቤዛነትን ሥራ ለመፈጸም መጣ። በዚህ ረገድ እንዲህ አለ፦ "የላከኝም ከእኔ ጋር ነው። አብ ብቻዬን አይተወኝምና፤ ሁልጊዜ ደስ የሚያሰኘዉን እሠራለሁና።" (ዮሐንስ 8: 29)። እንደ አገልጋይ፣ ለማገልገል መጣ። ስለዚህ፣ በማቴዎስ 20: 28 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጅ እንዲያገለግሉት አልመጣም ።"

በውጫዊ መልኩ፣ መሲሑ አገልጋይ ነበር፣ በውስጥ ግን አሁንም የክብር ጌታ ነበር።የታላቁ የመዳን ዕቅድ እንዲፈጸም ለእርሱ የሚያስፈለገዉ ሁሉንም ነገር መሆን ብቻ ነበር።

### ነቢዩ

ሐዋርያው ጴጥሮስ በዘዳግም 18: 18 ላይ የተነገረለትን መሲሕ ነቢይ መሆኑን ጠቅሷል። በሐዋርያት ሥራ 3: 22-23 ላይ እንዲህ ይላል፦ "ሙሴስ ለአባቶች፦ ጌታ አምላካችሁ ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይን ያስነሳላችኋል፤ የሚነግራችሁን ሁሉ ስሙት፤

ይህንም ነቢይ የማይሰማ ነፍስ ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ይጠፋል ብሎ በእውነት ተናገረ።" ጌታም የነቢይን ሥራ መፈጸም ነበረበት። ስለዚህም ያንን ነቢይ የማይሰማ ነፍስ ሁሉ እንዲጠፋ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። እግዚአብሔርን ለመስማትና ለማመን እንዲሁም የዘላለም ሕይወት ለማግኘት እርሱን መስማትና ማመን አለብን።

በመለወጥ ተራራ ላይ፣ ከሰማይ በላይ ከሆነው ደመና ድምፅ ተሰማ፡- "ይህ የምወደው ልጄ ነው፣ በእርሱም ደስ ይለኛል፤ እርሱን ስሙት። ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሰምተው በፊታቸው ወድቁ እጅግም ፈርተዉ ነበር።" (ማቴዎስ 17: 5-6)። የእግዚአብሔር ፍርሃት በእኛ ላይ ሲመጣ ብቻ ነው ለጌታ፣ ለቃሉና ለሚያደርገው ነገር ትክክለኛ አመለካከት የሚኖረን። ኢየሱስ ክርስቶስን በክብር ካየነው፣ "እርሱን ስሙት!" ለሚለው ቃል ትኩረት መስጠት አለብን። ማንኛውንም ተቋም፣ ቀሳውስት ወይም መንፈሳዊ ሥልጣን የመስማት ግዴታ የለብንም፤ እርሱን ብቻ እንድንሰማና እንድንታዘዝ ተነግሮናል።

እርሱ ጌታ ነበር፣ እንደ ነቢይ በመሆን የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ በ በእግዚአብሔር ፍጹም ቃል አማካኝነት ይገልጽ ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ፡- "አንተ ያ ነቢይ ነህን?" ተብሎ ተጠየቀ። እርሱም፡- "አይደለሁም" ሲል መለሰ (ዮሐንስ 1: 21)። ዮሐንስ ታላቁ ነቢይ ነበር፣ ምክንያቱም ብሉይንና አዲሱን ኪዳን አገናኘ፣ መሲሑንም እንደ እግዚአብሔር በግ አስተዋወቀ፣ ነገር ግን ሙሴ የተናገረለት ያ ነቢይ አልነበረም። ሙሴ የተናገረለት ያ ነቢይ መሲሑ ነበር። በእርሱ አማካኝነት፣ የመዳን ዕቅድ ትንቢታዊ ክፍል ታወቀና በአገልግሎቱ ተረጋገጠ። በዮሐንስ 6:14 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "እንግዲህ እነዚያ ሰዎች ኢየሱስ ያደረገውን ተአምር ባዩ ጊዜ፡- ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ ።"

የመሲሑ አገልግሎት ትንቢታዊ ክፍል ሊኖረው ግድ ነበር። እያንዳንዱ ቅዱሳት መጻሕፍት መፈጸም አለበት። እርሱ እንደ ነቢይ ከተነገረለት፣ እንደ ሌሎች ነቢያት ሁሉ በመለኮታዊ ተልእኮ እንደተላከ መናገር ነበረበት። ይህ ደግሞ እንደ ወልድ በተገለጠበት ጊዜ ከያዛቸው ተግባራት አንዱ ነበር። ስለዚህ፣ በዮሐንስ 5: 19 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ወልድ አብ ሲያደርግ ያየውን እንጂ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያንኑ ያደርጋል።"

እንደ ሰው ልጅ፣ ሰዉ መሆኑን ነቢያት እንዳደረጉት በተመሳሳይ መንገድ በማድረግ ገለጠ። እዚህ ላይ አቅመ ቢስ አምላክ ለኃያል አምላክ እንደ ሚናገር አልነበረም፣ ነገር ግን የሰው ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በነብይነት ተግባሩ ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነበር። ጌታ የላካቸው ነቢያት ባለ ራእዮች ነበሩ፤ በመንፈስ መለኮታዊ መነሳሳት ራእዮችን ያዩ ነበር፣ የእግዚአብሔርም ፈቃድ ለእነርሱ ይታወቅ ነበር። እዚህ ደግሞ **የሰው ልጅን** እናያለን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመፈጸም የነቢይነት፣ የባለ ራእይነት ቦታ ሲይዝ። እርሱ ያየውንና የሰማውን ተናገረ።

እንዲሁም በመዝሙር 40: 7-8 ላይ የተጻፈው የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እርሱን ያመለክታል፣ በዕብራውያን 10: 7-9 ላይ እንደተመዘገበው፡- "ከዚያም እንዲህ አልኩ፡- እነሆ እኔ መጣሁ… አምላክ ሆይ፣ ፈቃድህን ለማድረግ፡፡" ነቢያትና ብዙ ጻድቃን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ይፈልጉ ነበር፣ ነገር ግን ከሆነ ቦታ ላይ ወድቀዋል፡፡ እዚህ ሊወድቅ የማይችለው ብቸኛዉ እርሱ ነው፣ እርሱ ሊያደርገው አላሰበም ብቻ ሳይሆን፣ የማድረግ ኃይልም ነበረው፡፡ በዕብራውያን 10: 10 ላይ እንዲህ ይላል፡- "…በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል፡፡" እርሱ ፍጹም በግ ነበር – ፍጹም መሥዋዕት፣ በእርሱም ፍጹም ቤዛነት አለን፡፡

ከእግዚአብሔር እንደተወለደ ልጅ የመጀመሪያዉ አዳምን አለመታዘዝ አስወገደና ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ታዛዥነትን መሠረተ፡፡ እዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ ሊያደርግና ሊፈጽም ስለቻለ፣ እኛም አሁን የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ የማድረግ ቦታ ላይ ተቀምጠናል፡፡ እንደ ቆላስይስ 2: 13 ገለጻ ሙሉ ይቅርታን ተቀብለናል፡- "እናንተም በኃጢአታችሁና በሥጋችሁ አለመገረዝ ሙታን የነበራችሁትን፣ ከእርሱ ጋር ሕያዋን አደረጋችሁ፣ ኃጢአታችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ ፡፡" ሁላችንም ክርስቶስ ነቢይ መሆን እንደነበረበት እናውቃለን፣ ነገር ግን ከነቢይ በላይ ነበር፡፡ እርሱ በነቢያት ሁሉ የተናገረው ታላቁ **እኔ ነኝ** ነበር፡፡ እርሱ፡- "አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነኝ" ሊል የቻለው እርሱ ነበር (ዮሐንስ 8: 58)፡፡

## የእግዚአብሔር በግ

በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ በጉ ንፁህ መሥዋዕት ተብሎ ይታይ ነበር፣ ለጥፋተኛውን የሰው ዘር ለመሞት የሚመጣውን ፍጹሙን የእግዚአብሔር በግ ያሳያል፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ መሲሑ ሲመጣ ባየ ጊዜ ወደ እርሱ ጠቆመና፡- "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!" አለ (ዮሐንስ 1: 29)፡፡ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "ከአባቶቻችሁ በተቀበላችሁት ከንቱ የሕይወት ዘይቤአችሁ እንደ ብርና እንደ ወርቅ በሚጠፋ ነገር ሳይሆን፣ ያለ ነውርና ያለ እድፍ እንደሆነ እንደ በግ፣ በክርስቶስ ክቡር ደም እንደተቤዣችሁ ታውቃላችሁና" (1ኛ ጴጥሮስ 1: 18-19)፡፡

የሕያው አምላክ ቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑት በመለኮታዊ ደም ፍጹም በሆነ መንገድ ተቤዥተዋል (ሐዋርያት ሥራ 20: 28)፡፡ በሮሜ 3: 25-26 ላይ፣ ሐዋርያው ይህን ሀሳብ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡- "…በደሙ በሚሆን እምነት የማስተስሪያ መባ አድርጎ ያስቀመጠው፣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለቀድሞ ኃጢአቶች ስርየት፣ በእግዚአብሔር ታጋሽነት የተነሣ ሊገልጥ፤ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ሊገልጥ፣ እርሱም ጻድቅ እንዲሆንና በኢየሱስ የሚያምነንም የሚያጸድቅ እንዲሆን ነው፡፡" በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አማካኝነት ምንኛ ድንቅ እውነት ቀርቦልናል! ለሁሉም ጥያቄዎቻችን መልስ የሆነ ክርስቶስ አለን፡፡ በእምነት የሚያምኑት ይጸድቃሉ፣ ለዘላለምም ይቀደሳሉ፣ እርሱም ስለ እኛ ራሱን እንደቀደሰ (ዮሐንስ 17: 19)፡፡

## ካህኑ

መሲሑም የእምነታችን ሊቀ ካህን መሆን ነበረበት። በዕብራውያን 9: 11-14 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ " ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለዉ መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ ፤ በምትበልጠዉ እና በምትሻለዉ በእጆችም ባልተሰራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን ፤ የዘላለም ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጅ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም። የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ ከሆኑ፤ነዉር የሌለዉ ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያዉን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?" እንደ ካህን እርሱን መሥዋዕቱን የሚያቀርብ ሆኖ እናየዋለን። በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ በጉ፣ መሥዋዕቱ ራሱ ነበር። በምድራዊ ዘመኑ ይጸልይ ነበር። ይህ ትርዒት አልነበረም፣ ይህ ለሰው አስፈላጊ ነበር። በዕብራውያን ምዕራፍ 5፣ ከቁጥር 7 ጀምሮ እንዲህ እናነባለን፦ "...እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደ ሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከዕንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት፣ ምንም ልጅም ቢሆን  ከደረሰበት መከራ መታዘዝን ተማረ፤ ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህን ተብሎ ስለ ተጠራ ፤ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸዉ።" በሥጋ አካል ውስጥ ሰው ነበር፤ ተሠቃየ፤ ሙሉ በሙሉ ታዛዥ ነበር። ያ ሁሉ የታላቁ የቤዛነት ዕቅድ አካል ነበር። እኛ ራሳችንን መርዳት ስለማንችል እርሱ ለመርዳት መጣ።

ስለዚህ ምስጢራዊ መልከ ጼዴቅ በዘፍጥረት 14: 18 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ " የሳሌም ንጉስ መልከ ጼዴቅም እንጀራና የወይን ጠጅን አወጣ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር። ባረከውም እንዲህም አለ፦ ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነዉ ። አብርሃም የሰማይና የምድር ባለቤት ከሆነው ከልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፤ ከሁሉም አስራትን ሰጠው።" አንድ ሰው ይህን የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅስ ብቻ ካነበበ፣ በኢየሩሳሌም አንድ ንጉሥ እንደነበረ እና  የካህንነትን ሥልጣንም የያዘ እንደነበረ ሊያስብ ይችላል። በዕብራውያን ምዕራፍ 7 ላይ፣ ይህ ንጉሥና ካህን በትንሹ በቅርበት ተገልጿል፦ "...ለእርሱም አብርሃም ከሁሉም አስረኛውን ክፍል ሰጠ፤ አስቀድሞም የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው፣ ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥም ማለት የሰላም ንጉሥ ነው።አባት እና እናት የትዉልድም ቁጥር የሉትም፤ የዘመናት መጀመሪያም የሌለው፣ የሕይወትም ፍጻሜ የሌለው፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ዘወትርም ካህን ሆኖ ይኖራል።" (ቁጥር 2-3)።

"የጽድቅ ንጉሥ" እና "የሰላም ንጉሥ" ሊባል የሚችለው አንድ ብቻ ነው። እርሱም የነገሥታት ንጉሥ ነው። በአብርሃም ዘመን በሥጋ አካል ገና አልመጣም ነበር፤ ስለዚህ መጀመሪያ አልነበረውም። ለዚህም ነው በዚያ ግንኙነት አባትና እናት አልነበረውም የሚለው። ነገር ግን ሥጋ ከለበሰ ጀምሮ እንደ ልጅ ተወለደ፤ ስለዚህ አባትና እናት ሊኖረው ተገባ።

በምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ንጉሥ ወይም ካህን አባትና እናት አለው፣ ነገር ግን መልከ ጼዴቅ፣ የሰላም ንጉሥ፣ አልነበረውም። ይህ ደግሞ ለአብርሃም እንደ ካህን የመጣው ጌታ፣ በኋላ በዚህ ዓለም እንደ ወልድ እንደመጣ የሚያሳይ አስደናቂ ማስረጃ ነው። እንደ ካህን እንጀራና የወይን ጠጅ ይዞ ወደ አብርሃም መጣ፣ ይህም የጌታ እራት ምሳሌ ነው። በጠላቶች ላይ የተደረገውን ጦርነት ከአሸነፈ በኋላ፣ እራቱ ተደረገ። በቤዛነት ካገኙት ጋርም እንዲሁ ይሆናል። መንፈሳዊው ውጊያም ካለቀ በኋላ፣ ድሉን ያገኙት ከጌታ ጋር ወደ ታላቁ እራት ይወሰዳሉ።

በብሉይ ኪዳን፣ ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በታላቁ የኃጢአት ማስተስሪያ ቀን መግባት ይችላል (ዕብራውያን 9: 7)። ነገር ግን ክርስቶስ በራሱ ደም እንደ ሊቀ ካህን አንድ ጊዜ ብቻ ገባ፣ በዚህም ቤዛነታችንን አጠናቀቀ። ደሙ በዚህ የምድር አቧራ አልተመጠጠም፣ በዚህ ምድር ላይ ፈሰሰ፣ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፣ በራሱ ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገባና በምሕረት መቀመጫው ላይ አኖረው።

ከዚያን ቀን ጀምሮ፣ የእግዚአብሔር ምሕረት ሊቀበሉት ለሚፈልጉ ሁሉ ይገኛል። ደሙ ዛሬም ለእኛ ይናገራል። የአዲስ ኪዳን ደም ነው፣ ይህም በጸጋ ዘመን ለሚያምኑ ሁሉ የሚሰራ ነው። ይህ ደግሞ ኢሳይያስ በምዕራፍ 53: 10 ላይ የሰጠውን ትንቢት ያስታውሰናል፦ “ጌታ ግን በደዌ ያደቅቀዉ ዘንድ ፈቀደ ፤ ሐዘንንም አኖረበት። ነፍሱን ስለኃጢአት መሰዋት ከአደረገ በኋላ ዘሩን ያያል ፤ ዘመኑም ይረዝማል፣ የጌታም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል።”

## አስታራቂ እና ጠበቃ

ስርየት እና እርቅ የሚያመለክቱት አስታራቂን ወይም ጠበቃን ነው። በብሉይ ኪዳን ይህን ሐሳብ በጣም በግልጽ ያጎላው ኢዮብ ነበር። “ሆኖም ትክክለኛዉን መንገድ ለሰዉ ያመለክት ዘንድ ፤ መካከለኛም ይሆንለት ዘንድ ፤ ከሽህ አንድ መልአክ ቢገኝ ፤ ለሰዉየዉም በመራራት፤ ቤዛ አግኝቼለታለሁና፤ ወደ ጉድጓድ እንዳይወረድ አድነዉ ቢለዉ ፤ በዚህ ጊዜ ሥጋዉ እንደ ሕጻን ልጅ ገላ ይታደሳል ፤ ወደ ወጣትነቱም ዘመን ይመለሳል። ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል እርሱም ሞገስን ይሰጠዋል ፊቱንም በደስታ ያሳየዋል፤ ለሰዉም ጽድቁን ይመልስለታል።” (ኢዮብ 33: 23-26)።

ይህ ለአመኑት ለእነርሱ በትክክል ሁኗል። ዋጋው ተከፍሏል፣ እኛም ተቤዥተናል፣ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ እና ያለ ነውር ነን። ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የእርሱ የሆኑት አካላቸው ይለወጥና ፍጹም ወደሆነ የወጣትነት ዘመን ይመለሳሉ፣ በኢዮብ እንደተተነበየውም፣ ለዘላለምም እንደዚያው ይኖራሉ። አሜን።

ቀድሞውኑም በብሉይ ኪዳን የነበሩ ነቢያትና ጠቢባን ድነቱ እንዲከናወን ይጠባበቁ ነበር። ኢዮብ በሁሉም መከራውና ተስፋ በሌለበት ሁኔታ በእምነት እንዲህ ሲል ጮኸ፦ “የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነና በመጨረሻው ዘመን በምድር ላይ እንደሚቆም አውቃለሁና፤ ከቆዳዬም በኋላ ትሎች ይህን

አካል ቢያጠፉትም፣ በሥጋዬ ግን እግዚአብሔርን አያለሁ፣ ሌላ ሰዉ ሳይሆን እኔዉ በገዛ አይኔ፤ እኔ እራሴ አየዋለሁ፤ምንም እንኳ ልቤ በዉስጤ ቢቃጠልም ።" (ኢዮብ 19: 25-27)።

መሲሑን ከእግዚአብሔር በተጨማሪ በሁሉም የተለያዩ ባህሪያት ተገልጦ እናየዋለን። በዚህም ምክንያት፣ ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2: 5 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከልም አንድ አስታራቂ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ።" ሁለት አምላኮች አይደሉም፣ በመለኮት ውስጥ ሁለት አካላትም አይደሉም፣ ነገር ግን አንድ አምላክና አንድ አስታራቂ፦ ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ። የሰው ዘርን ለማዳንና ለመሞትና ደሙን ለቤተ ክርስቲያን ቤዛ አድርጎ ለማፍሰስ ሰው መሆን እንደነበረበት አንድ ጊዜ ለዘላለም መረዳት አለብን።

በዕብራውያን 12: 24 ላይ፣ ወደ "የአዲስ ኪዳን አስታራቂ ወደ ሆነዉ ወደ ኢየሱስ፣ እንዲሁም ከአቤል ደም የተሻለ ቃል ወደሚናገረውን ወደ ተረጨዉ ደም ደርሳችኂል" እንደመጣን ይናገራል። በራሳችን ዉስጥ መንፈሳዊ ሕይወት ውጤታማ ከመሆኑ በፊት ሁሉንም ነገር ማመን አለብን። ቀድሞውኑም በብሉይ ኪዳን አስታራቂዉ በነቢዩ በሙሴ አማካኝነት በግልጽ ተነግሮ ነበር፣ እርሱም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ቆሞ ነበር። በአዲስ ኪዳን፣ በሐዋርያት ሥራ 7: 38 ላይ በሚከተሉት ቃላት ተጠቅሷል፦ "ይህም በሲና ተራራ ከእርሱ ጋር በተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው፣ ሕያው የሆኑትን ቃላት ተቀብሎ የሰጠን ነው።" እግዚአብሔር ተናገረ፣ ሙሴም የተቀበለውን ቃል ለሕዝቡ የሚያደርስ ነበር። እርሱ እንደ አስታራቂ ሆኖ ሠራ።

የጠበቃ አገልግሎትም አስፈላጊ ነው። ዮሐንስ ለሚያምኑት እንዲህ ይላል፦ "ልጆቼ ሆይ፣ ኃጢአት እንዳትሠሩ ይህንን እጽፍላችኂለሁ። ማንም ግን ኃጢአት ቢሠራ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፣ እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እርሱም የኃጢአታችን ማስተስሪያ ነው፣ የእኛም ብቻ ሳይሆን በዓለሙ ሁሉ ኃጢአትም ነው።" እንደገና ከዚህ ክርስቶስን ከእግዚአብሔር አጠገብ እናያለን፣ ነገር ግን እንደ ሌላ አካል ሳይሆን፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለመዳን ዕቅድ አስፈላጊ ከሆኑት ተግባራት በአንዱ ውስጥ። እርሱም አሁን በሰማይ ከፍ ብሎ በግርማዉ ቀኝ እና ኃይል ተቀምጧል። ይህ በመዝሙር 110: 1 ላይ ተተንብዮ ነበር፦ "እግዚአብሔር ለጌታዬ እንዲህ አለው፦ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ።" እዚያም የመጨረሻዉ ጊዜ እስኪመጣ እና ሁሉም ነገር በእግሩ ሥር እስኪሆን ድረስ ይኖራል (ዕብራውያን 1: 13)።

## ማጠቃለያ

በአዲስ ኪዳን ዘመን ሁሉ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር በተጨማሪ ይታያል፤ ምንም እንኳን እንደ እግዚአብሔር ሁለተኛ አካል ሆኖ ባይሆንም፣ ሁልጊዜ ግን መፈጸም በነበረባቸው የአገልግሎት ተግባሮች ዉስጥ በአንዱ ሆኖ፣ ለምሳሌ እንደ ሰው ልጅ። እስጢፋኖስ  ወደ ሰማይ ሲመለከት፦

“እነሆ፣ ሰማያት ተከፍተው፣ **የሰው ልጅ** በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ።” (ሐዋርያት ሥራ 8: 56)። ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ነገሮች መሆን ነበረበት፡- የእግዚአብሔር በግ፣ ሊቀ ካህን፣ የሰው ልጅ ወዘተ፣ እንደአብራራነዉ። ከእግዚአብሐር በተጨማሪ በታየ ቁጥር፣ የታላቁ የመዳን ዕቅድ አስፈላጊነት መሠረት በተግባር ይታይ ነበር።

እኛ እንድንቤዥ እነዚህን ሁሉ ነገሮች መሆን ነበረበት። በዕብራውያን 12: 2 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “...የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ እንመልከት፣ እርሱ በፊቱ ስለነበረው ደስታ መስቀልን ታገሰ፣ ነውርንም ንቆ፣ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጧል።”

እስጢፋኖስ እንደ **ሰው ልጅ** ያየው ያው አካል፣ ዮሐንስ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ሲመላለስ አየው (ራእይ 1: 12-20)። እስጢፋኖስ እርሱን በሰማይ አየው፣ ዮሐንስ ደግሞ በምድር ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አየው። ያው አካል በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህን ነው (ዕብራውያን 4: 15)። እርሱ በምሕረት መቀመጫው ላይ ስለ እኛ የሚማልድ ጠበቃ ነው።

በሐዋርያት ሥራ 9: 3-6 ላይ እንደተመዘገበው፣ በደማስቆ መንገድ ላይ ለሳውል በደማቅ በሚያበራ ብርሃን ሊገለጥለት ችሏል። ሳውል፡- “ጌታ ሆይ፣ ማን ነህ?” ብሎ በጠየቀ ጊዜ፣ እርሱም፡- “የምታሳድደኝ ኢየሱስ እኔ ነኝ...” ሲል መለሰ። ታዲያ እርሱ ማነው? ምንድን ነው? የት ነው ያለው? አንዱ እርሱን እንደ ሰው ልጅ ከእግዚአብሔር አጠገብ በዙፋን ላይ ያየዋል፤ ሌላው ደግሞ በምሕረት መቀመጫው ላይ እንደ ሊቀ ካህን፣ ስለ እኛ ሲማልድ ያየዋል፤ ሌላው ደግሞ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ሲመላለስ ያየዋል። እና እንደገና፣ የሳውልን ዓይኖች ባሳወረ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ብርሃን ታየ።

ይህ ብቻ አይደለም፡- ዮሐንስ በጳጥሞስ ደሴት እያለ፣ እርሱን እንደ አሸናፊዉ የይሁዳ ነገድ አንበሳ ሆኖ እንዳየው ይዘግባል። ከዚያም እንደታረደ በግ አየው። የእርሱን መገለጦች መጥቀስ መቀጠል እንችላለን። ምንም እንኳ ብዙ ቢሆኑም፣ እርሱ ያው ነው። እነዚህ እርሱ ሊሠራቸው የነበሩ የተለያዩ ሚናዎች ነበሩ። ነገር ግን ወደ ጉዳዩ ዋና ነገር ስንመጣ፣ ፈለጉ ወደ ዘላለማዊው ጌታ እግዚአብሔር ይመልሰናል። በሚያስፈልጉት መገለጦቹ አናቆምም፣ አንድ ቀን፣ ሁሉም ነገር ሲፈጸም፣ እርሱን እንዳለ እናየዋለን። ጌታ እንደፈቀደ ራሱን ሊገልጥ ይችላል፣ ይህንንም ለማድረግ የማንንም ፈቃድ አይጠይቅም።

## የእግዚአብሔር ልጆች

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር የራሱን ዕቅድ የሚፈጽምበትን በጣም አስፈላጊ እውነታ እየተመለከትን ነው። እርሱ ግንኙነትን ለእኛ መመሥረት ነበረበት፤ ስለዚህም ለሰው ልጆች እንደ **ሰው ልጅ** ተገለጠ። በዕብራውያን 2: 6-9 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ታስበዉ ዘንድ ሰው ምንድር ነው ? ወይስ ትጐበኘዉ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሳነስኸው፤ የክብርና የምስጋና ዘዉድ አክሊል ጫንህለት፣ በእጆችህም ሥራ ላይ ሾምኸው፤ ሁሉንም ከእግሮቹ በታች

አስገዛህለት ብሎ መሰከረ። ሁሉንም ከእርሱ በታች ባስገዛ ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና። አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለ ገና አናይም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰዉ ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ፤ ከመላክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረዉን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሳ የክብር እና የምስጋናን ዘዉድ ተጭኖ እናየዋለን።" ይህ ሁሉ የሆነው በእኛ ምክንያት ነው። ለመሠቃየት፣ ለመሞት፣ ከሙታንም ለመነሳት፣ ወደ ክብርም ለመግባት እንዲችል እኛ ያለንበትን አካል መዉሰድ ነበረበት ። በዚህም፣ ለእኛ መንገድ ከፈተልን።

በዕብራውያን 2: 10-11 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ሁሉ ነገር ለእርሱ እና በእርሱ የሚኖር እግዚአብሔር ፤ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ለማምጣት፤የድነታቸዉን መስራች በመከራ ፍጹም ሊያደርገዉ የተገባ ነበር። ሰዎችን የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሰዎች ከአንድ ቤተሰብ ናቸው፣ ስለዚህ ኢየሱስ ወንድሞች ብሎ ሊጠራቸው አያፍርም።" ከትንሣኤው በኋላ ጌታ በመቃብር ለነበሩ ሴቶች ተናገረ፡- "አትፍሩ፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፤ በዚያም ያዩኛል"(ማቴዎስ 28: 10)።

እንዴት ድንቅ ሀሳብ ነው! የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሁሉም አንድ አባት አላቸው። በዚህም፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እኛን እንደ ልጆቹና ሴት ልጆቹ ወደ ራሱ የመመለስ ዓላማው እየተከናወነ ነው። ያው ሀሳብ በዮሐንስ 20: 17 ላይም ተረጋግጧል፡- "ኢየሱስም አላት፡- አትንኪኝ፤ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና። ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂጂ፣ እንዲህም በያቸው፡- ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ።"

በፍጻሜው፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደሚለወጡና የጌታችን የኢየሱስን እውነተኛ መልክ መስለዉ ይታያሉ ። ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጻፈ፡- "ወዳጆች ሆይ፣ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምን እንደምንሆን ግን ገና አልታየም፤ ነገር ግን እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ፣ እርሱን እንዳለ እናየዋለንና እንደ እርሱ እንደምንመስል እናውቃለን።" (1ኛ ዮሐንስ 3: 2)። እንደተጻፈው ሁሉ እውነት ነውና ይከናወናል። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምክር ይጸናል እና በእውነት የሚያምኑት የመጨረሻውን ፍጻሜ ያያሉ።

በመዝሙር 22: 22 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ስምህን ለወንድሞቼ እገልጻለሁ፤ በጉባኤ መካከልም አመሰግንሃለሁ።" ስሙ ለሁሉም ሰው አልታወቀም፣ ነገር ግን እንደተጻፈው፣ ራሱን ለወንድሞቹ ያሳውቃል። እነርሱም እግዚአብሔርን በሕጋዊ መንገድ የሰማይ አባታቸው ብለው የሚጠሩት ናቸው። ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን አማካኝነት ለእኛ ተሰጥቷል። "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰዉነት ተገልጦ ይኖራልና፤ እናንተም በሁሉም ራስ በሆነው በእርሱ ፍጹማን ናችሁ" (ቆላስይስ 2: 9-10)። ይህ ደግሞ እውነት ነውና በእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ውስጥ ይገለጣል።

ጌታችንን በሰዉ ልጅነቱ እናያለን፣ እርሱም ከቤዛነት ሥራ ጋር የተያያዙትን ሁሉንም የተለያዩ ገጽታዎች ሲሰራ። አንድ ተዋናይ የተለያዩ ሚናዎችን መጫወት እንዳለበት ሁሉ፣ እርሱም ለመዳናችን አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም ሚናዎች መጫወት ነበረበት። ቅዱሳት መጻሕፍትን

እንደተነገረን ስንፈልግ፣ እርሱ በሁሉም ዘረፍ እንደተገለጸ እናገኛለን። በብሉይ ኪዳን፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እርሱ ምን እንደሚሆን መስክረዋል። በአዲስ ኪዳን፣ የእርሱ ፍጻሜ ብቻ እንደሆነ ያሳያል። የዘላለም ሕይወት አለን የሚሉና በእውነት ዳግም እንደተወለዱ የሚያምኑት፣ ክርስቶስ በሁሉም የተለያዩ መገለጦችና አገልግሎቶች እንደሚታይ በመለኮታዊ መገለጥ በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ።

በዮሐንስ 17: 3 ላይ፣ በጣም አስፈላጊ የሆነ መግለጫ ይገኛል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "ይህም የዘላለም ሕይወት ነው፣ አንድ እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተን፣ የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ።" እንዳየነው፣ ክርስቶስ ከአምላክ በተጨማሪ ሌላ አምላክ ሆኖ አይታይም፣ ነገር ግን እርሱ በቀጥታ የአምላክ መገለጥ ነው፣ በዕብራውያን 1: 3 ሀ ላይ እንደተጠቀሰው፡- "...የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ፣ ሁሉንም ነገር በኃይሉ ቃል እየደገፈ..."። በዮሐንስ 6: 40 ላይ እንዲህ ይላል፡- "የላከኝ ፈቃድ ይህ ነው፣ ወልድንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ።" እግዚአብሔር በወልድ መገለጡ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ከሚከተሉት ቃላት መታየት ይቻላል፡- "በወልድ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን ሕይወትን አያይም" (ዮሐንስ 3: 36)።

ጌታ ለእኛ ታውቋል። በመጨረሻም ከሰዋዊዉ መጋረጃ ባሻገር ተመልክተን፣ ኢየሱስን ታላቁ አሸናፊ ሆኖ ስናይ ከቶማስ ጋር፡- "ጌታዬና አምላኬ!" ብለን እንመሰክራለን (ዮሐንስ 20: 28)። በሐዋርያው ጳውሎስ ምስክርነት መሠረት፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ እንደሆነ መመስከር የሚችሉት እውነተኛ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው ብቻ ናቸው። እርግጥ ነው፣ እንደ ጌታ እርሱ እግዚአብሔር ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 12: 3)።

እንደ መልካም እረኛ፣ ሕይወቱን ስለ በጎቹ ሰጠ። እንደ እግዚአብሔር በግ፣ ደሙን ለመዳናችን አፈሰሰ። እንደ ሊቀ ካህን፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገባ። እንደ ጠበቃ፣ ስለ እኛ ይማልዳል፣ ወዘተ፣ ወዘተ. እርሱም መንፈሳዊ ቤቱ፣ ቤተ ክርስቲያኑ፣ የተገነባበት የዋናው የማዕዘን ድንጋይ ነው (1ኛ ጴጥሮስ 2: 4-10)። ቤተ ክርስቲያን ስትጠናቀቅ እርሱ ራስ ይሆናል። እርሱ አልፋና ኦሜጋ ነው፣ ፊተኛውና መጨረሻው። እንደ ሰው ልጅ ነቢይ ነበር፤ እንደ ዳዊት ልጅ ንጉሥ ይሆናል፤ እንደ እግዚአብሔር ልጅ እርሱ የተቤዠን ነበር።

ከእግዚአብሔር በተጨማሪ ጌታን በብዙ መግለጫዎች የሚያይ ሁሉ፣ እነዚህ ነገሮች ከሰው ልጆች ጋር ያለውን የእግዚአብሔርን ታላቅ ዕቅድና ዓላማ ለመፈጸም አስፈላጊ እንደሆኑ ሁልጊዜ ማስታወስ አለበት። ጊዜ ወደ ዘላለም ሲዋሃድ፣ ሁሉም ነገር ያበቃል፣ እግዚአብሔርም ሁሉ በሁሉ ሆኖ እናየዋለን። የጸጋው ዘመን ካለቀ በኋላ፣ ከክርስቶስ ጋር ለአንድ ሺህ ዓመት እንነዛለን (ራእይ 20: 6)። ይህን ታላቅ ተስፋ በራእይ 3: 20-21 ላይ ለእኛ ሰጥቷል። ከሺህ ዓመቱ ግዛት በኋላ የነጩው ዙፋን ፍርድ ይሆናል፣ ከዚያም ጊዜ ወደ ዘላለም ይዋሃዳል።

## በዘመናት የሸመገለዉ

በዳንኤል 7: 9-10 ላይ እጅግ ልዩ የሆነ ክስተት ተመዝግቧል፦ "ዙፋኖች እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ፣ በዘመናት የሸመገለዉም ተቀመጠ፣ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር፣ የራሱም ፀጉር እንደ ንጹሕ ጥጥ ነበር፣ ዙፋኑም የእሳት ነበልባል ነበረ፣ መንኮራኩሮቹም የሚነድድ እሳት ነበሩ…" እግዚአብሔር በእርግጥ አያረጅም፣ እርሱ አያት አይደለም፣ እርሱ አባታችን ነውና ለዘላለምም የማይለወጥ አምላክ ነው። በዚህ ራእይ ዳንኤል እግዚአብሔርን ዳኛ ሆኖ አየዉ፤ በክብሩ ኣና በግርማዊ ጌትነቱ ዉስጥ ከፍተኛዉ የስልጣን ደረጃ ። ድልድዩ በቁጥር 13 ላይ ታይቷል። ዳንኤል እንዲህ አለ፦ "በሌሊት ራእይ አየሁ፣ እነሆም፣ የሰው ልጅ የሚመስል በሰማይ ደመና መጣ፣ ወደ ዘመናት ወደ ሸመገለዉም ደረሰ፣ ወደ ፊቱም አቀረቡት።"

እንዲህ ያሉት የመጻሕፍ ቅዱስ ጥቅሶች በአምላክ ውስጥ ብዙ አካላትን ለማረጋገጥ ያገለግሉ ነበር፣ ሆኖም ግን አስቀድመዉ በትንቢታዊ ራእይ የብሉይ ኪዳን ነቢያት በአዲስ ኪዳን የሚሆነውን እንደሚያዩ ሙሉ በሙሉ ከመርሳት የመጣ ነዉ ። ይህ ራእይ እስከ ዛሬ ድረስ አልተፈጸመም፦ " ወገኖች እና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛት እና ክብር መንግስትም ተሰጠዉ ፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነዉ ፤ መንግስቱም የማይጠፋ ነዉ " (ቁጥር 14)። ክርስቶስ እንደ ንጉሥ የሚነግሥበት ጊዜ ይመጣል፣ እኛም ከእርሱ ጋር። የዘመናት የሸመገለዉ መግለጫ ከሰው ልጅ ጋር ሲገጥም ብታዩ ትደነቃላችሁን? ይህን ለማረጋገጥ በራእይ ምዕራፍ 1፣ ከቁጥር 13 ጀምሮ እናነባለን፦ "…በሰባቱ መቅረዞችም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለዉን አየሁ፣ እርሱም እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰዉ ፤ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር። ራሱና የራስ ፀጉሩም እንደ ነጭ የበግ ጠጉር እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፤ ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ…"።

አዲስ ኪዳን ላይ የምንጠቀምባቸውን ቃላቶች ብንጠቀም፣ በቀላሉ ዳንኤል ነጭ ፀጉር ያለውን አብን አየዉ፣ ዮሐንስም ነጭ ፀጉር ያለውን ወልድን አየዉ እንላለን። ሁለቱም መግለጫዎች እጅግ ተመሳሳይ ናቸው። ይህ ደግሞ ወልድ የአብ መገለጥ እንደሆነና በመጨረሻም በእግዚአብሔር ውስጥ እንደገና እንደሚዋሐድ ያረጋግጣል፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15: 28 ላይ እንደተገለጸው፦ "ሁሉ ከተገዛለትም በኋላ፣ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን፣ ወልድ ራሱም ሁሉን ከእግሩ በታች ላስገዛለት ይገዛል።" ይህ በጣም ግልጽ ነው።

ወልድ የሌለበት ጊዜ ነበር፣ ነገር ግን በምትኩ ጌታ ነበር፤ አሁን ደግሞ እንደ ወልድ አለ፣ ከዚያም እንደገና ጌታ ይሆናል። ዮሐንስ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል እንደ **ሰው ልጅ** ሲመላለስ ያየው ያው አካል፣ በሚከተሉት ቃላት የራሱን ምስክርነት የሚሰጠው እርሱ ነው፦ "ያለዉና የነበረዉ የሚመጣዉም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ ፦ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።" (ራእይ 1: 8)። ጌታ የራሱን ምስክርነት ከመስጠቱ በፊት፣ ዮሐንስ በራእይ ሲመጣ አየው፦ "እነሆ፣ በደመና ይመጣል፣

ዓይንም ሁሉ ያየዋል፣ የወጉትም ደግሞ ያዩታል፤ የምድር ወገኖችም ሁሉ ስለ እርሱ ያለቅሳሉ፤ አዎን፣ አሜን።" (ቁጥር 7)።

በራእይ ምዕራፍ 20፣ ከቁጥር 11 ጀምሮ፣ የነጩ ዙፋን ፍርድ ታይቷል። በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው አንድ ብቻ ነበር፤ በፊቱም ሁሉም ሊሰበሰቡ ነው። ዮሐንስ እንዲህ ሲል ይመሰክራል፡- "ታላቅ ነጭ ዙፋንንም አየሁ፣ በእርሱም የተቀመጠውን፣ ከፊቱም ምድርና ሰማይ ሸሹ፣ ለእነርሱም ስፍራ አልተገኘላቸውም። ሙታንንም፣ ታላቆችንና ታናሾችን፣ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው አየሁ…"።

በራእይ ምዕራፍ 22፣ የእግዚአብሔርንና የበጉን ዙፋን እናነባለን (ቁጥር 1+3)፣ ነገር ግን እርሱን እንደ ሰው ስንገልጽ፣ በእርግጥ በነጠላ ቁጥር ይነገራል (ቁጥር 4)፡- "…ፊቱንም ያያሉ (ፊቶቻቸውን ሳይሆን)፤ ስሙም (ስማቸው ሳይሆን) በግንባራቸው ላይ ይሆናል።" በመጨረሻም በመጀመሪያ የተናገረው እንደገና ይሰማል። በመጨረሻው መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ እንዲህ ሲል ሲናገር እንሰማዋለን፡- "እነሆም፣ በቅርቡ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ያሜጋ፣ መጀመሪያዉ እና መጨረሻው እኔ ነኝ።" (ራእይ 22: 12-13)።

ማንም ሰው በዚህ የማያልቅ ርዕስ ላይ ብዙ መጽሐፍት ሊጻፉ እንደሚችሉ ያውቃል። እነዚህ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እያንዳንዱ ሰው በጸሎት የራሱን ፍለጋ እንዲያደርግ ለመርዳት ነው። የምናምነውንና የምናስተምረውን ሁሉ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ወሰን ውስጥ መቆየታችንን ማረጋገጥ አለብን። ሁሉም ነገር ሲጠናቀቅ፣ አዳኝ፣ ፈዋሽ፣ አማላጅ፣ ጠበቃ – የሚለው አያስፈልግም – ሁሉም እንደገና ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉና ለዘላለም ፍጹም ይሆናሉ። ያን ጊዜ ስለ ሰው ልጅ፣ ስለ ዳዊት ልጅ፣ ስለ እግዚአብሔር ልጅ – አንሰማም – እግዚአብሔር በቀላሉ ሁሉ በሁሉ ይሆናል።

በራእይ 21: 3-7 ላይ የሚገኘው መግለጫ ከዚህ አጭር ማብራሪያ ጋር እንደ ማጠቃለያ ተሰጥቷል፡- "እነሆ፣ የእግዚአብሔር ድንኳን ከሰዎች ጋር ነው፣ ከእነርሱም ጋር ይኖራል፣ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፣ እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር ይሆናል፣ አምላካቸውም ይሆናል። እግዚአብሔርም እንባን ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ሐዘንም፣ ዋይታም፣ ሥቃይም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀድሞዎቹ ነገሮች አልፈዋልና። በዙፋኑም የተቀመጠው እንዲህ አለ፡- እነሆ፣ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ። እርሱም፡- ይህ ቃል እውነትና የታመነ ነውና ጻፍ አለኝ። እርሱም፡- ተፈጸመ አለኝ። እኔ አልፋና ያሜጋ፣ መጀመሪያዉ እና መጨረሻዉ እኔ ነኝ። ለተጠማም ከሕይወት ውኃ ምንጭ በነፃ እሰጠዋለሁ። ድል የነሳ ሁሉ ሁሉንም ይወርሳል፣ እኔም አምላኩ እሆናለሁ፣ እርሱም ልጄ ይሆናል።"

ይህ ቡክሌት የአለ ክፍያ ቀርቧል ፡፡ ተጨማሪ ኮፒዎች ለተመረጡ ስርጭቶች በጥያቄ ሊላኩ ይችላሉ ፡፡

ማንም ስለሌሎች መንፈሳዊ ርዕሰ ጉዳዮች ማወቅ የሚፈልግ በነጻነት ሊጽፍልን ይችላል ፡፡ እንደ እነዚህ አይነቶች “ ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚ“ ፤ “ ክርስትና ትናንት እና ዛሬ“ ፤ “እግዚአብሄር እና ከእኛ ጋር ያለዉ እቅዱ“ ፤“ጥምቀት ፤የጌታ እራት “ “ ተጽፏል “ እና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡

በምእራብ ጀርመን ክሪፌልድ በሚገኘዉ አለም አቀፋዊ የሚሲዮን ማዕከል በጀርመን ቋንቋ እና በእንግሊዘኛ እናትማለን፡፡ ይህ የእምነት ስራ ቤተእምነታዊ ያልሆነ ከሁሉም የክርስቶስ አካል ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡አላማችን የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ማሳወቅ እና የዘመናችንን እድገቶች ወደ መጻህፍ ቅዱሳዊ ትንቤቶች መፈጸም ብርሃን ለማምጣት ነዉ፡፡

እናንተን ለማገልገል ደስተኞች ነን

**አድራሻችን**

**ተልዕኮ ማዕከል** Mission Center

**የፖስታ ሳጥን** P.O. Box 100707

47707 Krefeld

Germany

E-mail: volksmission@gmx.de or E.Frank@freie-volksmission.de

Homepage: http://www.freie-volksmission.de